ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 307 ሐምሌ 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# የግብርና ወጪ ንግዱ ፈተናዎች

አዲሱ ገረመው

በግብርና ምርቶች ወጪ ንግድ ላይ ያተኮሩ አዳዲስ የቁጥጥር ሕጎች እየወጡ ነው። ኢትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸው የግብርና ምርቶች ላይ በአዳዲስ ዓለም አቀፍ የደኅንነት፣ የቁጥጥርና የፍተሻ ሕጎችን የእራሳቸውን አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደግ ጀምረዋል።

በተለይ ከፍተኛ ቴክኖሎጂንና አቅምን የሚጠይቁ የጥራትና የደኅንነት መስፈርቶችን እንዲሁም ተያያዥ ግዴታዎችን የሚጥሉ የቁጥጥር ሕጎች የግብርና ወጪ ንግዱ ላይ ስጋት ሆነዋል። ሕጎቹ የተነደፉት ወደ ውጪ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን

የግብርና ወጪ ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



መስፍን አርዓያ (ፕ/ር)

# ኮሚሽኑ በድሬዳዋና በሦስት ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራ ሊጀምር ነው

## -በ10 ክልሎች የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ ተጠናቋል

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ በአራት ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራ እንደሚጀምር የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ይፋ አደረገ፡፡ በ10 ክልሎች የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ መጠናቀቁም ተገልጿል፡፡

የኮሚሽኑ ዋና ሰብሳቢ መስፍን አርዓያ (ፕ/ር)፤ ምክክር ኮሚሽኑ የመጀመሪያውን አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በስኬት ማካሄዱን አስታውሰዋል።

በመጪው ሳምንት በአራት ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብና የማወያየት ተግባር ይጀምራል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣

ኮሚሽኑ በድሬዳዋና...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያ የጤና ዋስትናው የተረጋገጠ ሠራዊት ለመገንባት ትኩረት ሰጥታለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የጤና ዋስትናው የተረጋገጠ ሠራዊት ለመገንባት ትኩረት ሰጥታ እየተሠራች ነው ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት የምስራቅ ዕዝ ደረጃ ሦስት ሪፈራል ሆስፒታል በክሊኒካል ነርሲንግ በደረጃ አራት ያሠለጠናቸውን ሙያተኞች ትናንትና አስመርቋል።

ኢትዮጵያ የጤና ዋስትናው...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “አመራሩና ሕዝብ ተናቦ መሥራት ከቻለ ከተማን መለወጥ እንደሚቻል አዲስ አበባ ማሳያ ናት”

## -የተለያዩ ከተማ ከንቲባዎች

ገጽ 4


















ዜና



ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር

# ኪነጥበብን ለበጎ ዓላማ በመጠቀም ለሀገር አንድነትና እድገት መሥራት ይገባል

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- ኪነጥበብን ለበጎ ዓላማ በመጠቀም ለሀገር አንድነትና እድገት መሥራት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ የኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የኪነጥበብና ቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ምሥረታና አንደኛ መደበኛ ጉባኤ ትናንትና አካሂዷል።

በጉባኤው መክፈቻ የክብር እንግዳ የሆኑት የአዲስ አበባ ምክር ቤት አፈጉባኤ ቡዜና አልቃድር እንደገለፁት፤ ኪነጥበብን ለበጎ ዓላማ በመጠቀም ለሀገር አንድነትና እድገት ማዋሉ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው።

ኪነጥበብ የአንድ ኅብረተሰብ የእድገትና የሥልጣኔ ደረጃ የሚንፀባረቅበት እንዲሁም ከሰው ልጆች ስሜት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው ዘርፍ ነው ብለዋል።

ኪነጥበብና ዴሞክራሲ በአንድ ላይ ተያይዘው እንዲያድጉ ባለድርሻ አካላት ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ መሥራታቸው አስፈላጊ መሆኑንም ተናግረዋል።

እንደ አፈጉባኤዋ ገለፃ፤ አዲስ አበባ ከተማ ከለውጡ ማግስት በተሠሩ በርካታ የቱሪዝም ሥራዎች የበርካቶች መዳረሻ መሆን ችላለች።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ የኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ካለፉት አምስት የለውጥ ዓመታት ጀምሮ በባሕል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ዘርፎች በርካታ ሥራዎችን መሥራት መቻሉን ጠቁመዋል።

ቢሮው ጠቃሚ የባሕል እሴቶችንና ሀገር በቀል እውቀቶችን በማጠናከር መጤ ባሕሎችን ለማስቀረት የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን ሲሰጥ መቆየቱን ተናግረው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከበሩ ሕዝባዊና ባሕላዊ በዓላት በተሻለ ደረጃ እንዲከበሩ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱንም አንስተዋል።

በተጨማሪ የከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻዎች ለማሳደግና የቱሪስት ፍሰቱ ከፍ እንዲል መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቁመዋል።

ከጉባኤው ጎን ለጎን የቱሪዝም አዋርድና አምባሳደር ተሰይሟል። በሁለገብ የኪነጥበብ ባለሙያነትና በበጎ አድራጎት ተግባሯ የምትታወቀውን አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ የአዲስ አበባ ከተማ የቱሪዝም አምባሳደር ሆና ተሰይማለች። በተጨማሪ በስድስት ዘርፎች በተለያዩ የቱሪዝም ተግባራት በመሳተፍ ላይ ለሚገኙ ተቋማት የቱሪዝም ሽልማት አበርክቷል።

በባለ አምስት ኮኮብ ሆቴሎች ዘርፍ ለውድድር ከቀረቡት ስምንት ሆቴሎች ካፒታል ሆቴል የመጀመሪያ ደረጃ በመያዝ ተሸላሚ ሆኗል። በባለ አራት ኮኮብ ሆቴሎች ዘርፍ ደግሞ ሳሮማሪያ ሆቴል የመጀመሪያ ደረጃን ይዟል። በባሕላዊ የምግብ አዳራሽ ዘርፍ ዮድ አቢሲኒያ የባሕል ምግብ አዳራሽ ቀዳሚ ደረጃ ይዞ ተሸልሟል።

በተጨማሪም በቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ሰጭዎች ዘርፍ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርቶች ድርጅት በአንደኛነት አሸናፊ ሆኗል።

ተሸላሚ ተቋማትን የመለየቱ ተግባር ኮሚቴ ተዋቅሮ ለአንድ ዓመታት ያክል እንደተሠራበት ተጠቁሟል። የእውቅናና ሽልማት የመስጠት ሥነ-ሥርዓቱ በየዓመቱ እንደሚከናወን በጉባኤው ተመላክቷል።

በመድረኩ የኪነጥበብና ቱሪዝም ዘርፍ አጀንዳዎች ቀርበው ውይይት ተደርጓል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ዣንጥራር አባይ፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በጉባኤው ተሳትፈዋል።

# ከ586 ሚሊዮን ዶላር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ለማልማት ውል ገብተዋል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከ586 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ያስመዘገቡ 48 ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮችና ወደ ድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣና ገብተው ለማልማት የውል ስምምነት መፈራረማቸውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የኮርፖሬሽኑ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዘመን ጁነዲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለሀብቶቹ ውል ከመፈጸማቸው ባለፈ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ቅድመ ኦፕሬሽን ሥራዎች አከናውነዋል።

ባለሀብቶች ወደ ፓርኮችና ድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ገብተው እንዲያለሙ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል ሲሠራ ቆይቷል ያሉት አቶ ዘመን፤ ስምምነቱን ከፈፀሙት 48 ባለሀብቶች መካከል 90 በመቶ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች መሆናቸውን አንስተዋል።

ከ52 ሄክታር በላይ የለማ መሬትና ከ94 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ስፋት ያላቸው 16 የማምረቻ ሼዶች ለባለሀብቶች መተላለፋቸውን አስታውቀው፤ የውል ስምምነቱን የፈረሙ ኩባንያዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ ሲገቡ ከ16 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ ብለዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በሚያስተዳድራቸው የኢንቨስትመንት ማዕከላት ተኪ ምርቶችን ከማምረትና ምርቶችን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚወጣን የውጪ ምንዛሪ ለማዳን በርካታ ሥራዎችን እያከናወኑ ነው ያሉት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የቢራ ገብስ ብቅል ሙሉ ሙሉ በሀገር ውስጥ መተካት እንደተቻለ ጠቁመዋል።



አቶ ዘመን ጁነዲን

የተለያዩ የፀጥታ አካላት የደንብ ልብስ፣ የፌዴራልና የክልል እንዲሁም የኮርፖሬሽኑን ጨምሮ የበርካታ ተቋማትን ብራንድ አልባሳት በፓርኮች ውስጥ እየተመረቱ መሆኑን አስረድተዋል።

አቶ ዘመን እንዳመላከቱት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ሀገር በቀል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ የማበረታቻ ሥርዓቶች ተዘርግተዋል።

ቀደም ሲል ሀገር በቀል ባለሀብቶች የማምረቻ ሼድና የለማ መሬት ኪራይ በዶላር እንዲከፍሉ ይገደዱ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ በብር እንዲከፍሉ ተደርጓል ብለዋል።

በሌላ በኩል ሀገር በቀል ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገቡ ይከፍሉ የነበረውን 10 በመቶ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ወደ አምስት በመቶ ዝቅ መደረጉም ከማበረታቻዎች መካከል መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት ተግባራዊ ያደረገውን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም መነሻ በማድረግ በኮርፖሬሽኑ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ተሳትፎን ለመጨመር ሲሠራ መቆየቱን ገልጸው፤ በተደረጉ የአሠራር ማሻሻያዎች የሀገር በቀል አምራቾችን ድርሻ ከ10 በመቶ ወደ 53 በመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

በቅርቡም በኮርፖሬሽኑ ስር በሚተዳደሩት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙና የለሙ መሬቶችን ለመጠቀም "መሬታችን ለባለሀብቶቻችን" በሚል መሪ ሃሳብ የንቅናቄ መርሐ ግብር መጀመሩን አመላክተው፤ በዚህም ከፍተኛ የሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ፍሰት እየታየ ነው። ይህም አሁን ያለውን ድርሻ ይበልጥ ከፍ ያደርገዋል ብለን እንጠብቃለን ብለዋል።

በተያያዘ የአጎዋ የነፃ የንግድ ገበያ እድል በመታገዱ ምክንያት የኤክስፖርት አቅማቸው ደከም ያሉ ጥቂት ኩባንያዎች ነበሩ ያሉት አቶ ዘመን ጁነዲን፤ አሁንም የአሜሪካን ገበያ በቀረጥ ክፍያ እየተጠቀሙ ያሉ በርካታ ኩባንያዎች መኖራቸውን አብራርተዋል።

ከዚህ ውጪ ግን እንደኮርፖሬሽን ኢንቨስተሮች ከሚጠቀሙባቸው የዓለም ገበያዎች በተጨማሪ አማራጭ የገበያ መዳረሻዎችን እየተፈለጉ መሆኑን አንስተው፤ አሁንም በሩቅ ምሥራቅ፣ በአውሮፓ እና በእንግሊዝ የገበያ መዳረሻዎች ላይ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በፓርኮቻችን የሚመረቱ ምርቶች ደረጃቸውን የጠበቁና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆናቸው በየትኛውም ዓለም ላይ በደንበኞች እና በገዢዎች ተመራጭ ናቸው ሲሉ አቶ ዘመን ጁነዲን አስረድተዋል።

# አሽከርካሪዎችና እግረኞች በክረምቱ ወራት ጥንቃቄያቸውን ሊያሳድጉ ይገባል

ዮርዳኖስ ፍቅሩ



አዲስ አበባ፡- አሽከርካሪዎችና እግረኞች በክረምቱ ወራት ለትራፊክ አደጋ ከሚያጋልጡ ድርጊዎች በመቆጠብ ጥንቃቄያቸውን ሊያሳድጉ እንደሚገባ የመንገድ ደኅንነትና መድኅን ፈንድ አገልግሎት አሳሰበ።

በመንገድ ደኅንነትና መድኅን ፈንድ አገልግሎት የመንገድ ደኅንነት ትምህርትና አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዮሐንስ ለማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክረምት ጊዜ የአየር ንብረት እርጥበታማ እንደመሆኑ የአሽከርካሪዎችና እግረኞች እንቅስቃሴ ወቅቱን ያገናዘበና ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባል፡፡

የክረምት ጊዜ ዝናባማና ጭጋጋማ በመሆኑ መንገዶች በዝናብ በሚርሱበት ጊዜ ጎማ የማንሸራተት ባሕሪ ሊያመጡ እንደሚችል ጠቁመው፤ አሽከርካሪዎችም ተሽከርከሪዎቻቸውን ለመቆጣጠርና መንገዳቸውን በአግባቡ ለማየት የሚቸገሩበት ወቅት በመሆኑን ሊጠነቀቁ እንደሚገባ አቶ ዮሐንስ ተናግረዋል፡፡

የክረምት ወቅት ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ለትራፊክ አደጋ አጋላጭ ሁኔታዎች የሚጨምሩበት በመሆኑ በተለይም፣ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎቻቸውን ከማስነሳታቸው አስቀድመው የቴክኒክና የኤሌክትሪክ ደኅንነቱን በሚገባ መመልከት ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

እንደአቶ ዮሐንስ ከሆነ፤ አሽከርካሪዎች ለእንቅስቃሴ አስቸጋሪ የሆነ ዝናብ በሚኖርበት ጊዜ መኪናቸውን በተፈቀደላቸው ቦታ በማቆም ሊፈጠር የሚችለውን የትራፊክ አደጋ በመቀነስ የበኩላቸውን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በማንኛውም ጊዜ ከፊት ካለው ተሽከርካሪ የሦስት ሰከንድ ርቀት ሊኖር ይገባል የሚለውን ሕግ በአግባቡ መተግበር፣ የዝናብ መጥረጊያ መኖሩንና በአግባቡ መሥራቱን እንዲሁም የግራና የቀኝ የትዕይንት መከታታያ መስታወት መኖሩን ማረጋገጥ ከአሽከርካሪዎች የሚጠበቁ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሆናቸውንም አቶ ዮሐንስ አመላክተዋል።

በተሽከርካሪ መንገዶች ላይ ማየትም ሆነ መታየትም ከአደጋ ለመጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ የተሽከርካሪ መብራቶች በትክክል መሥራታቸውን ማረጋገጥም የሚጠበቅ ቅድመ ጥንቃቄ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በተለይም ወቅቱ በተለያዩ አካባቢዎች የ12ተኛ ክፍል ተፈታኞች የመልቀቂያ ፈታና ለመውሰድ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት በመሆኑ፣ ተማሪዎች ደኅንነታቸው ተጠብቆ በሠላም ወደየመጡበት እንዲመለሱ ከማድረግ አኳያ አሽከርካሪዎች ኃላፊነት እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡

አሽከርካሪዎች ማድረግ ያለባቸው ጥንቃቄ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እግረኞችም ራሳቸውን ከትራፊክ አደጋ ለሚያጋልጡ እንቅስቃሴዎች መጠበቅ እንዳለባቸውም አቶ ዮሐንስ አንስተዋል፡፡

ፊትን በተለይም እይታን በጃንጥላ ከልሎ መንቀሳቀስ፣ ከዝናብ ለማምለጥ ሲባል ግራና ቀኝ ሳያስተውሉ አስፋልት መሻገር፣ የጆሮ ማዳመጫ እየተጠቀሙ መንቀሳቀስ የመሳሰሉ ለአደጋ አጋላጭ ልምዶች በእግረኞች ዘንድ እንደሚስተዋሉ የዘረዘሩት አቶ ዮሐንስ፣ የእግረኛ መንገድ አጠቃቀም ሕግን አክብሮ በመጓዝ ዜጎች ራሳቸውን ከአደጋ በመጠበቅ እንዲንቀሳቀሱ መልዕክት አስተላልፈዋል።

አቶ ዮሐንስ እንዳስታወቁት፤ መንገድ የጋራ መጠቀሚያ ቦታ እንደመሆኑ አሽከርካሪዎችም ሆነ እግረኞች መንገድን በአግባቡና በጥንቃቄ መጠቀም ከቻሉ ከትራፊክ አደጋ የተጠበቀ ማኅበረሰብን መፍጠር ይቻላል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## "ከመጀመሪያው ስህተት የሁለተኛው" እንደሚባለው እንዳይሆንብን!

የስፖርት ጉዳይ ከስፖርትነት ያለፈ ትርጉም ከተላበሰ ዓመታት ተቆጥረዋል። በተለይም የኦሊምፒክ ስፖርት ከመዝናኛነት ባለፈ የብሄራዊ ክብር እና ኩራት ምንጭ በመሆን፤ ሀገራት ለውድድር መድረኩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው፤ ሰፊ ጊዜ እና ሀብት መድበው ውጤታማ ለመሆን በቁርጠኝነት እንዲንቀሳቀሱ እያስገደዳቸው ነው።

በውድድር መድረኩ የሚመዘገቡ ውጤቶችም፤ ሀገራትን እንደ ሀገር በአደባባይ ከፍ ያለ ክብር እና ሞገስ የሚያጎናጽፍ፤ ሰንደቅ ዓላማቸው እና ብሔራዊ መዝሙራችው በአደባባይ ጎልቶ እና ደምቆ እንዲታይ ፤ እንዲሰማ የተሻለ ታሪካዊ ዕድል የሚፈጥር፤ ዜጎች በዓለም አቀፍ መድረኮች አንገታቸውን ቀና አድርገው መሄድ እንዲችሉ የሚያስችልም ነው። በሀገር ገጽታ ግንባታም አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው።

በመድረኩ የሚገኝ ውጤት በብዙ ድካም እና ልፋት፤ በብዙ የሀገር ፍቅር እና ከዚህ በሚመነጭ የይቻላል መንፈስ የሚገኝ ነው፤ ሰፊ የዝግጅት ምዕራፍ የሚፈልግ፤ የስፖርተኛውን ብቻ ሳይሆን የስፖርት ባለሙያውን፤ የስፖርት አመራሩን፣ የመንግስት እና የመላውን ሕዝብ ርብርብ የሚጠይቅ ነው።

በተለይም የስፖርተኛውን ብቃት፣ የአሸናፊነት ስነ ልቦና ለመገንባትም ሆነ ውጤታማነትን ተጨባጭ ለማድረግ የስፖርት አመራሩ ድርሻ ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ አመራሩ ስፖርቱ ለሚገዛበት ሕግ እና ስርዓት ታማኝ መሆንና ለዚያ የሚሆን ስብእና ማጎልበት ይጠበቅበታል።

የኦሊምፒክ የስፖርት መድረክ ለኛ ለኢትዮጵውያን ከስፖርት ያለፈ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው፤ ከቀደሙት ጊዜያት ጀምሮ የብሔራዊ ክብራችን አንዱ መገለጫ ነው። ዛሬ ዜጎች መድረኩን እንደ አንድ የብሄራዊ ክብር መገለጫ አድርገው ይጠብቁታል። በመድረኩ ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ ብሎ ሲውለበለብ እና ብሔራዊ መዝሙራችን ሲሰማ ማየትና መስማትን ይናፍቃሉ።

አበበ በቂላ በሮም በባዶ እግሩ፣ በቶኪዮም ጫማ አጥልቆ፤ ማሞ ወልዴ በሜክሲኮ፣ ምሩፅ ይፍጠር በሞስኮ፣ ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ በባርሴሎናና ሲድኒ፣ ሻላቃ ኃይሌ ገብረስላሴና ፋጡማ ሮባ በአትላንታ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ገዛኸኝ አበራ፣ ሚሊዮን ወልዴ በአቴንስ፣ ጥሩነሽ ዲባባና መሰረት ደፋር በቤጂንግና ለንደን፣ አልማዝ አያና በሪዮ፣ ሰለሞን ባረጋ በቶኪዮ ያስመዘገቡዋቸው ድሎች ፤ ከስፖርት ውድድር ድል በላይ ከሀገር አልፈው ለጥቁር ሕዝቦች የመንፈስ ልዕልና ያጎናጸፉ፤ ወደ ፊትም ለሚመጡ ትውልዶች የተመሳሳይ የመንፈስ ልዕልና ምንጭ የሚሆኑ ናቸው።

ከፊታችን ያለውን የ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ውድድርን ስናስብም፤ ይህንን እውነታ ታሳቢ ባደረገ፤ በዚህ ደረጃ የሚመዘን ዝግጁነት እየፈጠርን መሆን አለበት። ከዚህ ውጪ የሆነ ዝግጁነት፤ ሊመጣ የሚችለውም ውጤቱ የቱንም ያህል ከፍ ያለ ቢሆን፤ በራሱ ምሉዕ ሆኖ በመድረኩ ያለንን የተወዳዳሪነት እና የአሸናፊነት ታሪክ ሊያስቀጥል አይችልም ።

አሁን ላይ ያለው ሀገራዊ የኦሊምፒክ ዝግጅታችን፤ በአንድም ይሁን በሌላ ችግሮች ሊኖሩበት፤ ለችግሮቹ እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ የሕግ፣ አሰራር፣ የአመለካከት ..ወዘተ ክፍተቶች ሊኖሩም ይችላል። ከቀረን ጊዜ አንጻር ያለን አማራጭ በችግሮቹ እና በምንጮቻቸው ዙሪያ መነታረክ ሊሆን አይገባም።

ከዚህ ይልቅ ባለችው ጊዜ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ካሉ በሰከነ መንፈስ፣ አሸናፊነትን እና አሸናፊነቱ በስፖርቱ መድረክ ሊያጎናጽፈን የሚችለውን ብሔራዊ ክብር ታሳቢ ባደረገ መንገድ ማረም እና ማስተካከል ላይ ቅድሚያ ሰጥተን ልንቀሳቀስ ይገባል።

አሁን አደባባይ የሞላው ጭቅጭቅ እና ንትርክ ከሁሉም በላይ እንደ ሀገር ሊጎዳን የሚችለው እኛን ነው። በጭቅጭቅ እና በንትርክ የምንፈታው ችግር የለም፤ ከዚያ ይልቅ መረጋጋት መስከን ያስፈልገናል "ከመጀመሪያው ስህተት የሁለተኛው "እንደሚባለው ስህተት ለማረም በሚል የበለጠ ስህተት እንዳንሰራ መጠንቀቅ ይጠበቅብናል።

ሌላውን ሁሉ ለሌላ ጊዜ አስቀምጠን አሁን ከሁሉም በላይ አትሌቶቻችንን የአሸናፊነት መንፈስ በሚያጎለብት፤ የይቻላል መንፈስን በውስጣቸው ሊያሰርጽ እና ሊያጸና በሚችል መንገድ ላይ ቆመን ልንደግፋቸው፤ ልናበረታታቸው እና ተጨማሪ የጉልበት ምንጭ ልንሆናቸው ይገባል። ድል ለኢትዮጵያ !


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ቅድሚያ ለሀገር ሞገስ ለሚሆን ውጤት !

አሜን ከካምቦሎጆ

የ2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ ሊጀመር ከሁለት ሳምንት ያነሰ ጊዜ ቀርቶታል። በዚህ ዓለም በጉጉት በሚጠብቀው ትልቅ የስፖርት መድረክ ከመካከለኛ እስከ ረጅም ርቀት እንዲሁም ማራቶን ድረስ ስሟን የሚያስጠሩ ከዋክብት አትሌቶች አጥታ የማታውቀው ኢትዮጵያ ውጤታማ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁ አገራት ቀዳሚ ነች።

ሀገሪቱ በኦሊምፒኩ ከፍ ብላና በውጤት አሸብርቃ ለመታየት እንቁ አትሌቶችን ታድላ ያጣችው ነገር ባይኖርም በዚህ ወቅት ትኩረቷ ውድድሩ ላይ ሳይሆን ፤ ባለፉት ዓመታት እንደተስተዋለው በአስተዳደራዊ ንትርኮች ላይ መሆኑ ግን በብዙ መልኩ ዜጎችን እያነጋገረ ይገኛል ።

በአሁኑ ሰዓት በኦሊምፒክ የሚሳተፉ ከሁለት መቶ በላይ አገራት ድምፃቸውን አጥፍተው ውጤታማ የሚያደርጓቸው ስራዎች ተጠምደዋል። ከነዚህ አገራት መካከል በተለያዩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የሚነታረክና ውዝግብ ውስጥ የሚገኝ አንድም አገር ፈልጎ ማግኘት አይቻልም።

እኛ ግን ዓለም ሁሉ የሚቀናባቸው አትሌቶችን ታቅፈን ለዚህ አልታደልንም ። ትኩረቱ ሁሉ አገር በታላቁ የስፖርት መድረክ ከዚህ ቀደም ከነበራት የተሻለ ውጤት እንዴት ታስመዝግብ ሳይሆን ስፖርቱን የሚመሩ አካላት በፈጠሩት ዝርክርክ አሰራርና አስተዳደራዊ ጉዳይ ላይ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ለችግሩ መነሻ የሆነው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመራሮች ከሕግና ከመርህ ባፈነገጠ አካሄድ የፈጠሩት ቀውስ ነው። ሁለቱን የስፖርት ተቋማት የሚመሩ ግለሰቦች ብዙ ነገሮችን ስተዋል። እያንዳንዱን ነገር በዝርዝር ለማየት ጊዜ አለ። አሁን ግን ውድድሩ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ቀርተውታልና በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ሆነን አትሌቶቻችን እንዴት ውጤታማ ይሁኑ የሚለው ጉዳይ ላይ ማተኮሩ ተገቢ ነው።

> **ለችግሩ መነሻ የሆነው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመራሮች ከሕግና ከመርህ ባፈነገጠ አካሄድ የፈጠሩት ቀውስ ነው**

ለዚህም አንገብጋቢ በሆነውና የበርካታ እንቁ አትሌቶቻችንን እንባ እያፈሰሰ ትልቅ የሞራል ጉዳትም እያደረሰ የሚገኘው የአትሌቶች ምርጫ ዋጋ እንዳያስከፍለን በጥንቃቄ ማየት ያስፈልጋል። እንደ አለመታደል ሆኖ ነው እንጂ በዚህ ወቅት አገራችንን በታላቁ መድረክ እንዴት አጉልተን እናሳይ እንጂ የአትሌቶች ምርጫ ጉዳያችን ሊሆን አይገባም ነበር።

ያም ሆኖ በመርህ ሳይሆን በግለሰቦች ፍላጎትና በጥቅም ትስስር የሚመራው ኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአንድ አትሌት ላይ የፈፀሙትን በደል ያስተካከሉ መስሏቸው የነካኩት ነገር ሁሉ ለሌሎች በርካታ አትሌቶች በደል ምክንያት እየሆነ ይገኛል። ወትሮም ከሕግና ደንብ ውጪ የሚሰራ ነገር አንዴ ከእጅ ካፈተለከ ውጤቱ የከፋ እንደሚሆን ለማንም የሚደበቅ አይደለም ።

የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ዓላማም ፤ አስራ አንደኛው ሰዓት ላይ ሆነን ቢሆን፤ ቢያንስ ከዚህ በኋላ ሌላ ቀውስ እንዳይፈጠር እና ችግሩ የአገርን ውጤት ገደል ይዞ እንዳይወርድ ምን ይደረግ የሚለው ላይ ነው።

አሁን ላይ ሁላችንም እንደምንሰማው፤ ቀደም ሲል በተለያዩ ውድድሮች ይሳተፋሉ ተብለው ይፋ የተደረጉ አትሌቶች ሁለቱ የስፖርት ተቋማት መሪዎች በሚፈጥሯቸው ችግሮች በየቀኑ እየተፐወዙ፣ ቦታ እየቀተቀያየሩ ይገኛሉ። ትናንት በቋሚነት ይወዳደራል የተባለ አትሌት ዛሬ ተጠባባቂ ሲሆን፣ አትወዳደርም የተባለ አትሌት ደግሞ ድንገት ነጭ ላቡን እያፈሰሰ ለወራት ሲዘጋጅ በቆየ ሌላ አትሌት ሲተካ እያየን ነው።

በዚህ ርቀት ትሳተፋለህ ተብሎ ለወራት ሲዘጋጅ የቆየ አትሌትና አሰልጣኝ ድንገት የተዘጋጀበት ቀርቶ ባላሰበው ርቀት ትሮጣለህ ይባላል። የተቋማቱ አመራሮች ጩኸት ሲበዛባቸው የአንዱን እንባ አበስን ብለው የሌሎችን እያፈሰሱ ነው። በዚህም አትሌቶች፣ አሰልጣኞችና ክለቦች ቅሬታዎቻቸውን እየገለፁ ይገኛሉ።

አሁን ላይ በየትኛውም ርቀት ኢትዮጵያን በኦሊምፒክ ወክሎ ለመወዳደር እየተዘጋጀ የሚገኝ አትሌትም ይሁን አሰልጣኝ በተረጋጋ ሁኔታ ትኩረቱን ዝግጅቱ ላይ ብቻ አድርጎ እየሰራ አይደለም። ይህም አስፈላጊውን ዝግጅት ከማስተጓጎሉ በስነ-ልቦናም ረገድ ትልቅ ችግር መፍጠሩ አልቀረም።

የአትሌቶቹን ምርጫ በየጊዜው እየቀያሩ የሚገኙት የሁለቱ ተቋማት አመራሮች ችግር በዚሁ ቢያበቃ ጥሩ ነው። እንደ አያያዛቸው ግን አይመስልም፤ ድንገት ውድድሩ ሰዓታት ሲቀሩት የሚቀይሩት ሃሳብ ሊኖር እንደሚችሉ መገመት ሞኝነት አይመስለኝም። ለዚህ ደግሞ ባለፉት ዓመታት ውድድሮች ላይ የነበረውን ተሞክሮ ማስታወስ በቂ ነው።

ይህ አካሄድ በኦሊምፒኩ አገርን ዋጋ እንደሚያስከፍልና ውጤት እንደሚያሳጣ ለመናገር የስፖርት ተንታኝ መሆን አይጠይቅም። የሁለቱ የስፖርት ተቋማት አመራሮችም ይህን የሚያጡት አይመስለኝም። በዚህ ባለቀ ሰዓት ላይ ሆነው እንኳን ቢያንስ ተጨማሪ ስህተት ላለመስራት መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል።

ባለፉት ዓመታት በተመሳሳይ የስፖርቱ አመራሮች ንትርክና ውዝግብ ውጤት ሲጠፋ "ኦሊምፒክ መድረክ ላይ መሳተፍ በራሱ ስኬት ነው፣ እኛ ነን የብርና የነሐስ ሜዳሊያ የምንንቀው፣ የእኛን ውጤት ያላገኙ ብዙ አገራት ይቀኑብናል" የሚል የስላቅ መልስ ከተጠያቂነት ማምለጫ ነበር።

ዘንድሮ ግን ይሄን መስማት የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም ። እኛ መገለጫችን ወርቅ ነው። እኛ የአበበ ቢቂላ፣ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ጥሩነሽና መሰረትን የመሳሰሉ ከዋክብቶች መፍለቂያ እንጂ ሌላ አይደለንም። አሁንም ኢትዮጵያ እነዚያን ዘመን የማይሽራቸው የኦሊምፒክ ፈርጦች ያፈራ ማህፀኗ ለምለም ነው።

አገራቸውን በደምና ላባቸው ውድ ዋጋ ከፍለው ከፍ ማድረግ የሚችሉ አቅሙም ብቃቱም ያላቸው ብዙ ወጣት ከዋክብት አላጣችም። ሳታጣ ያጣችው ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ በቅንነት ስፖርቱን የሚመሩ ሰዎችን ነው። እነዚህ ሰዎች ኦሊምፒክ ለኢትዮጵያ ምን ማለት እንደሆነ በቅጡ የተረዱት አይመስልም፡፡

ኦሊምፒክ የኢትዮጵያውያን አልሸነፍ ባይነት፣ ጀግንነት የሚገለጥበት፣ በገንዘብ የማይተመን ገፅታ መገንቢያ፣ አንገታችንን ቀና አድርገን የምንሄድበት ሌላም ሌላም መሆኑን ስተዋል። ይድነቃቸው ተሰማን የመሳሰሉ ከኢትዮጵያ አልፈው ለአፍሪካ ስፖርት እንደ አባት የሚቆጠሩ በስፖርት አመራርነት የተከበሩ ሰዎችን ማፍራት በቻለች ሀገር እንዲህ አይነት የአመራር ጉራማይሌ መታየቱ ብዙዎችን የሚያሳዝን ነው።

እዚህ ላይ ሊታሰብበት የሚገባ ዋንኛ ጉዳይ ከየትኛውም ግለሰብ ማንነት በስተጀርባ የሚገኝ ለሀገር ጥቅም እና ብሄራዊ ክብር ያልተገዛ ስብእና በምንም መልኩ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል ነው። እንዲህ አይነቱ ስብእና ሊፈጥረው የሚችለው ጥፋት የታሪክ የሞራል እና የሕግ ተጠያቂት ይዞ እንደሚመጣም ማሰብ ተገቢ ነው።

# “አመራሩና ሕዝብ ተናቦ መሥራት ከቻለ ከተማን መለወጥ እንደሚቻል አዲስ አበባ ማሳያ ናት”

## -የተለያዩ ከተማ ከንቲባዎች

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- አመራሩና ሕዝብ ተናቦ መሥራት ከቻለ ከተማን ለነዋሪዎች ምቹ ማድረግ እንደሚቻል አዲስ አበባ ጥሩ ማሳያ ናት ሲሉ የተለያዩ ከተማ ከንቲባዎች ገለጹ፡፡

የተለያዩ ከተማ ከንቲባዎች ሰሞኑን የመዲናዋን የኮሪደር ልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

የጂግጂጋ ከተማ ከንቲባ ሻፊ አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አመራርና ሕዝብ በተቀናጀ መንገድ መሥራት ከቻሉ ከተማን ለነዋሪዎች ምቹ በማድረግ መለወጥ እንደሚቻል በአዲስ አበባ ማየት ተችሏል፡፡

በከተማዋ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሠሩ የኮሪደር ልማት ሥራዎች ለሕዝብና ሀገር ተስፋ ሰጪ ናቸው ያሉት ከንቲባው፤ ከመዲናዋ ልምድ በመውሰድ በጂግጂጋ ከተማ የአካባቢውን ፀጋ መሠረት በማድረግ ልማቱን ተግባራዊ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ በርካታ ጊዜያት ይባክኑ እንደነበር ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክትን በአጭር ጊዜና በጥራት ሠርቶ ለአገልግሎት በማብቃት አዲስ ባሕል መፍጠር መቻሉን ተናግረዋል፡፡

የጂግጂጋ ከተማ ከለውጡ በፊት 10 ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር ብቻ የአስፋልት መንገድ እንደነበራት አስታውሰው፤ ከለውጡ በኋላ 38 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ መሠራቱን አስታውቀዋል።

የደብረ ብርሃን ከተማ ከንቲባ በድሉ ውብሸት በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቶችን መጀመር ብቻ ሳይሆን ጥራትን ማዕከል በማድረግ የማጠናቀቅ ሂደት እየተፈጠረ




መምጣቱን ከአዲስ አበባ መመልከት ተችሏል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት በማደግ ላይ ላሉ የሀገሪቱ ከተሞች ልምድ መሆን የሚችል የተቀናጀ ልማት ነው ያሉት አቶ በድሉ፤ በልማቱ የእግረኛና መኪና መንገዶችን፣ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎችን፣ የመዝናኛ ቦታዎችንና ሕፃናትን ታሳቢ ያደረጉ ልማቶችን ተመልክተናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በደብረ ብርሃን ከተማ የኮሪደር ልማት ዲዛይን እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ የአዲስ አበባን ተሞክሮ በመውሰድ ከተሞችን ፅዱና ለነዋሪዎች ምቹ ለማድረግ እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡

ከለውጡ ወዲህ የፕሮጀክቶች የሥራ ባሕል ተለውጦ በታቀደላቸው ጊዜና ጥራት እየተጠናቀቁ እንደሚገኙ የገለጹት ከንቲባው፤ በተለይም የአመራሩ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች የተጠናከሩ በመሆናቸው ፕሮጀክቶች ሌሊት ጭምር እየተሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የመዲናዋ አመራር ተቀናጅተው ባለፉት ወራት ተግባራዊ ያደረጉት የኮሪደር ልማት ለከተሞች ትልቅ ተሞክሮ የሚሆንና ትምህርት የሚሰጥ ነው ያሉት ደግሞ የአዳማ ከተማ ከንቲባ ኃይሉ ጀልዴ ናቸው፡፡

የኮሪደር ልማቱ አመራር ከወሰነና ካቀናጀ ሕዝቡ ሥራውን ተቀብሎ ከተማን መለወጥ እንደሚቻል የተማርንበት የስኬታማ ሥራ ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ልማቶቹ የተናበቡ፣ ጥራት ያላቸውና በፍጥነት የተሠሩ መሆናቸው ለሌሎች ከተሞች አርዓያ የሚሆኑ ናቸው ብለዋል፡፡

ከአዲስ አበባ የተገኘውን ልምድ በመውሰድ በአዳማ ተጨባጭ ሁኔታ አሻሽለው ተግባራዊ እንደሚያደርጉ በመግለጽ፤ በተለይም አመራርና ሕዝብን በማቀናጀት ከተማን መለወጥና ሕዝብን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን እንደሚሠሩም አመላክተዋል።

ቀደም ሲል ልማቱ ዜጎች ያላሳተፈ በመሆኑ ነዋሪዎች ጉዳዮችን ወደ ፍርድ ቤት ሲወስዱ መቆየታቸውን ጠቅሰው፤ በአሁኑ ሕዝብ በልማቱ እያመነ በመምጣቱና ተጠቃሚ በመሆኑ ችግሮችን እያስቀሩ መሄድ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

# ኢትዮጵያ የጤና ዋስትናው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በምረቃው ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ዘመናዊ የጤና ተቋማትን በመገንባት የሠራዊቱን የጤና አገልግሎት ፍላጎት ለማሟላት በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያን የሚመጥን ዘመናዊ ሠራዊት ለመገንባት እየተደረገ ያለው ጥረት ግቡን የሚመታው በሁሉም ዘርፍ እየተደረገ ያለውን ጥረት በትምህርትና ሥልጠና መደገፍ ሲቻል ነው ብለዋል።

ተመራቂዎች በቆይታቸው ያገኙትን ዕውቀት ተጠቅመው ሠራዊቱን በቅንነት በታማኝነትና በኃላፊነት ማገልገል እንደሚገባቸውም አሳስበዋል።

የጤና ዘርፉን በአደረጃጀት እና በሰው ኃይል በማጠናከር እና በቁሳቁስ በማሟላት የሠራዊቱን የጤና ዋስትና ለማረጋገጥ የተጀመሩ ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ገልጸዋል።

የምስራቅ ዕዝ የደረጃ ሦስት ሪፈራል ሆስፒታል ኃላፊ ኮሎኔል ብርሃኑ ዘውዱ እንደገለፁት፤ ተመራቂዎቹ ከሁሉም የመከላከያ ዕዝ የተመለመሉ የሠራዊት አባላት ናቸው።

የአገር መከላከያ ሠራዊት በጤናውም ሆነ በሌሎች የሙያ መስኮች በራሱ አቅም እያሳደገ መሆኑን ጠቅሰው የዛሬዎቹ ተመራቂዎች የዚሁ ማሳያ ናቸው ብለዋል።

ተመራቂዎቹ በድሬዳዋ በሚገኘው የምሥራቅ ዕዝ ደረጃ ሦስት ሆስፒታል ትምህርታቸውን ለሁለት ዓመታት ከስድስት ወራት በንድፍ ሀሳብ እና በተግባር የተከታተሉና በደረጃ አራት በዲፕሎማ መመረቃቸውን ተገልጿል።

በዕለቱ ከተመረቁት 800 የሚጠጉ የጤና ባለሙያዎች ውስጥ 168ቱ ሴቶች መሆናቸው ተጠቁሟል።

በምርቃ መርሐ ግብሩ ላይ የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላና ሌሎች የሠራዊቱ ከፍተኛ መኮንኖች እንዲሁም የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ከድር ጁሐር ተገኝተዋል።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በሥልጠናው ብልጫ ላመጡ ተመራቂዎችና ለሥልጠናው መሳካት አስተዋፅዖ ለነበራቸው አካላት ሽልማት ሠጥተዋል። ፊልድ ማርሻሉ እና ከፍተኛ አመራሮች የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር አካሂደዋል፤ በሪፈራል ሆስፒታሉ የተሠሩ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችንም ጎብኝተዋል።

# ኮሚሽኑ በድሬዳዋና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሐረር፣ በጋምቤላ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት እንደሚጀመር አስታውቀዋል።

ኮሚሽነሮች ምደባ በማካሄድ በአንድ ጊዜ ወደ አራት ክልሎች የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራው እንደሚሠራ ገልጸው፤ የክረምቱ ሁኔታ ካላስቸገረ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በአብዛኛው ክልሎች አጀንዳ የማሰብሰብ ሥራው እንደሚጠናቀቅ አመላክተዋል።

በአፋር ክልል በዚህ ወቅት ሙቀቱ እየበረታ የሚሄድበት ወቅት ነው ያሉት ዋና ሰብሳቢው፤ ሙቀቱ እየቀነሰ ሲመጣ በሚቀጥለው ዓመት መስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱን ለማድረግ መታሰቡን አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት አንዳንድ ክፍተቶች መኖራቸውን አስታውሰው፤ ከተማዋ ሠፊ እንደመሆኗ የነበረውም ጊዜ አጭር ስለነበር ለተሳታፊ ጥሪ በሚደረግበት ወቅት ክፍተቶች መፈጠራቸውን ታዝበናል ሲሉ አንስተዋል።

በዚህም የሃይማኖት ተቋማትን ሙሉ በሙሉ ወደምክክሩ በማምጣት ሂደትና ታዋቂ ሰዎችን ወደ ስብሰባው በማቅረብ ሂደት ላይ በተወሰነ ደረጃ ክፍተቶች ነበሩ ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ የተፈጠሩ ክፍተቶችን ማኅበረሰቡ እንዲረዳና በቀጣይ ለማስተካከል ጥረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

በቀጣይ በክልሎች በሚደረገው አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት ካለፈው ትምህርት በመውሰድ የተሻለ ነገር ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ዋና ሰብሳቢው እንደተናገሩት፤ የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ በ10 ክልሎች የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በአማራ እና በትግራይ ክልሎች ላይ ቀሪ ሥራዎች መኖራቸውን አመላክተ ዋል።

በተጨማሪ በሱማሌ ክልል የተሳታፊ ልየታና መረጣ በሚደረግበት ወቅት በሁለት ዞኖች ላይ ባጋጠመው የጤና ችግር ምክንያት ችግር መፈጠሩን ጠቁመው፤ አሁን ላይ አንድ ኮሚሽነር እና ባለሙያዎች ተልከው የተሳታፊ ልየታ እያደረጉ መሆኑን አስታውቀዋል።

በአማራ ክልል በተወሰነ መልኩ የተባባሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በምዕራብ ኦሮሚያና አማራ ክልሎች በትጥቅ ትግል ላይ ላሉ አካላት የሠላም ጥሪ እየቀረበ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በትግራይ ክልል የተሳታፊ ልየታ ለማድረግ ሁኔታውን የማመቻቸት ሥራ እየተሠራ እንደሆነ የተናገሩት ዋና ሰብሳቢው፤ በየትኛውም ጊዜ ከክልሉ ጥሪ በሚያቀርብበት ወቅት ሥራው እንደሚጠናቀቅ አስረድተዋል፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን እንዳመላከቱት፤ ኮሚሽኑ የሚሠራ ቸውን ሥራዎች ለማጠናቀቅ ዘጠኝ ይቀሩታል። ቀሪ ተግባራትን በውጤታማነት ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

በቀጣይ ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ ሁሉም ዜጎች በሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የኮሚሽኑ ዋና ሰብሳቢ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የግብርና ወጪ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከወራሪ ተባዮችና በሽታ አምጪ ተሕዋሲያን ከሚመጡ ስጋቶች ለመጠበቅ ነው። ይሁንና ትግበራቸው በኢትዮጵያ የግብርና ኢንዱስትሪ ላይ ውስብስብ ሁኔታዎችን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዳለ ሀብታሙ እንደሚገልጹት፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል የሆኑ 185 ሀገራት ማንኛውም የግብርና ምርት ወደ ውጭ ሲወጣና ሀገር ውስጥ ሲገባ እርስበርሳቸው የሚቆጣጠሩበትን ዘዴን ተቀብለው ውሳኔውን በ1952 ዓ.ም ወደተግባር መለወጥ ችለዋል።

ይህ ውሳኔ የሰው ልጅ ወደ ውጭ ሀገር ሲሄድ ያለ ፓስፖርት መሄድ እንደማይችለው ሁሉ ማንኛውም የግብርና ምርት ወደ ውጭ ሲሄድ ያለ ፍተሻ የምስክር ወረቀት መሄድ አይችልም ከሚል እሳቤ ይመነጫል ሲሉ ያስረዳሉ።

የግብርና ምርት ተፈትሾ የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ከበሽታ፣ ከተባይ፣ ወይም ከማንኛውም አይነት ተዋሕሲያን ነፃ መሆኑ ተረጋግጦ ነው የሚሉት አቶ ወንዳለ፤ ይህ ወደ ሀገር ቤት የሚገቡትንም ሆነ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ የዓለም ንግድ ሥርዓት የሚመራበት ባለ 47 አንቀጽ የዕፅዋት ደኅንነት ፍተሻ ሕግ በተለይ ከዕፅዋት ጤንነትና ከምርት ኤክስፖርት አንጻር ትልቅ ሚናን እየተጫወተ ይገኛል። ይህንን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያ ወደ አውሮፓም ይሁን ወደ ሌሎች የዓለም ክፍሎች የግብርና ምርቶቿን መላክ ችላለች።

ሆኖም በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የግብርና ምርቶች ደኅንነት ላይ ያተኮሩ ተጨማሪ ሕግጋት ፈታኝ እየሆኑ መጥተዋል ብለዋል።ለአብነትም አሁን ላይ የአውሮፓ ገበያ በርካታ ሕጎችን ያወጣ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ደግሞ “ጫካ ከተጨፈጨፈ ቡና አንገዛም” እስከ ማለት የደረሰ ውሳኔ አንዱ መሆኑን ያነሳሉ።

ከዚህ በተጨማሪ አውሮፓውያኑ ምርት ከሚጓጓዝበት ትራንስፖርት አኳያም ጥብቅ ሕጎችን እያወጡ መሆኑን ጠቅሰዋል። ከሦስት ዓመታት በኋላ ማዳበሪያን ጨምሮ የኢትዮጵያ የኬሚካል አጠቃቀም በ50 በመቶ እንዲቀንስ የሚያስገድዱ ሕጎችን የማውጣት ሀሳብ እንዳላቸውም አቶ ወንዳለ አንስተዋል፡፡

እነዚህና መሰል በርካታ ሕግጋት የኢትዮጵያን የግብርና ምርት ስለሚጎዳ ሁሉም ሰው ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን አሟልቶ እንዲሠራ ግንዛቤው ሊኖረው ይገባል ይላሉ።

የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ በበኩላቸው፤ ማንኛውም የግብርና ውጤት ተመርቶ ለውጪ ገበያ ሲቀርብ የቁጥጥርና ደኅንነት ፍተሻ ሥርዓት እንደሚደረግ ጠቅሰው፤ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ከሌለ እንደ ሀገር በዘርፉ መወዳደር አደጋች መሆኑን ይገልጻሉ። በአሁን ወቅት ዋና ዋና በሚባሉ የገበያ መዳረሻዎች የተለያዩ ሕጎች እያወጡ እንደሚገኝ ይናገራሉ።

የአበባ ምርት ኢንዱስትሪ ላይ የአውሮፓ ኮሚሽን “የእሳት እራት” ከሚባል ተባይ ጋር ተያይዞ ያስተላለፈው ውሳኔ መኖሩንም ለአብነት አንስተዋል።ተባዩ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳለና በኢትዮጵያ የግብርና ምርት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ባይኖረውም በአውሮፓ ኅብረት በኩል የአንዳንድ የአውሮፓ ሀገራት የግብርና ምርትን ሊያጠቃ ይችላል በሚል እሳቤ የወሰዷቸው ርምጃዎች መኖራቸውን ነው ያስረዱት፡፡

ከዚህ ቀደም በምርቶቹ ላይ የነበረውን አምስት በመቶ ቁጥጥርና ፍተሻ (ኢንስፔክሽን) ወደ 25 በመቶ እንዳሳደጉና ይህ መሻሻል ካልቻለ የፍተሻ መጠኑ እየጨመረ እንደሚሄድ እንዲሁም በንግድ ልውውጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን እንደሚፈጥር ነው አቶ ቴዎድሮስ የተናገሩት።

ሌሎች ሀገራትም በተመሳሳይ የሚያስቀምጧቸው የዕፅዋት ጤንነት ፍተሻ መስፈርቶች መኖራቸውን ገልጸው፤ እንደ ሀገር በእነዚህን ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቶ በአግባቡ ካልተሠራበት አጠቃላይ የግብርና ኢንዱስትሪው ችግር ውስጥ ሊገባ ይችላል ነው ያሉት። ይህንን በሚመለከት ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በተለይም እንደ ኔዘርላንድ ካሉ ሀገራት ማየትም ተገቢ እንደሆነ ነው ያመላከቱት።

ጉዳዩን ሲያብራሩም፤ ኔዘርላንድ ትልቅ የሆርቲካልቸር ተቀባይ ሀገር ነች።ወደ70 በመቶ የአበባ ምርታችን ተቀባይ በመሆኗ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የንግድ ትስስርም ትልቅ ነው። በሀገሪቷ የሚገኙ የግብርና የምርምር ተቋማት ስመ ጥር እንደመሆናቸው የተሻለ ልምድ ማግኘት ይገባል ይላሉ። ተሞክሮዎቹ ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡ እየተሠራ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ከሆነ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ የሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪው በትሪሊየን ዶላር የሚቆጠር ይደረግበታል። እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ከአትክልትና ፍራፍሬ በዓመት የምትጠቀመው ከ100 ሚሊዮን ዶላር ባይበልጥም፤ በአበባ ምርት ግን ሰፊውን ገበያ መፍጠር ችላለች፡፡

ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሃብት ዕድል በሰፊው ለመጠቀም በየጊዜው እየተጠናከረ የመጣውን ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ማሟላት እንዳለባት አስገንዝበዋል፡፡

እንደ ሀገር ከዕፅዋት ፍተሻ ጋር በተገናኘ ያለውን አቅም መገንባት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ እስካሁን ባለው ግምገማ በመንግሥትም ሆነ በግሉ ዘርፍ በቂ ግንዛቤ እንደሌለ ይናገራሉ።ከዚህ አንጻር ግንዛቤ መፍጠር ላይ ሰፊ ሥራ መሥራት እንዳለበትና የአሠራር ሥርዓቶን በመዘርጋት በዓለም አቀፍ መስፈርቶች መሠረት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል ብለዋል።

አቶ ወንዳለ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ባለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት የዓለም ንግድ መጠናከር የግብርና ምርቶችን ከድንበር ተሻግረው እንዲዘዋወሩ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። ይህም በአካባቢ ሥነ-ምሕዳርና ኢኮኖሚ ላይ ስጋት የሚፈጥሩ ተባዮችንና በሽታ አምጪ ተሕዋስያን ላይ በጥብቅ እንዲሠራ አድርጓል፡፡

የግብርና ምርትን ሊያጠቁ የሚችሉ በሽታዎች፤ በነፍሳት፣ በአይጥ፣ በባክቴሪያ እና በቫይረሶች አማካኝነት ሊከሰቱ እንደሚችሉና፤ እያንዳንዱም በሰብል፣ በከብትና በሰው ጤና ላይ ጭምር ልዩ አደጋዎችን እንደሚፈጥር ያብራራሉ፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ጭማሪ እያሳየ ያለው የዓለም አቀፍ ንግድና የጉዞ ሂደት አንዱና ዋነኛው የተባይ መስፋፋት ዘዴ ነው ያሉት አቶ ወንዳለ፤ የሸቀጦች፣ የሰዎችና የግብርና ምርቶች እንቅስቃሴ ተባዮችን ከአካባቢያቸው አርቆ ወደ አዲስ አካባቢ በማጓጓዝ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርሱ ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ ዕፅዋትንና የዕፅዋት ምርቶችን የሚጎዳ የማንኛውም ዝርያ በሽታ አምጪ ወኪል ተባይ ስርጭት በመባባስ ላይ ይገኛል።ኢትዮጵያም ጥብቅ የደኅንነት ቁጥጥር ርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባትና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየወጡ ያሉ ሕግጋትን መከተል እንደሚገባት ነው ያመላከቱት።

በዘርፉ ይበልጥ ካልተሠራ የግብርና ምርት ኤክስፖርት ትልቅ አደጋ እንደሚያጋጥመው፤ ኤክስፖርቱ እመርታዊ ለውጥ እንዲያመጣ የሚታለሙ ነገሮች ሁሉ የምርት ተቀባይ ሀገራትን የደኅንነትና ጥራት መስፈርት እንዲያሟሉ በትብብር መሥራት እንደሚገባ ነው ባለሙያዎቹ ያሳሰቡት።

ነፃ ሃሳብ

# ከኢትዮጵያ

## በበለጠ ለሶማሊያ ሕዝብ ዋጋ የከፈለ ማን አለ ?

**እስማኤል አረቦ**

ሶማሊያ ባለመረጋጋትና በግጭት ውስጥ የምትኖር ሀገር ነች። ከዚያም አልፎ መንግስት አልባ ሆና ዘመናትን ተሻግራለች። በእነዚህ የመከራ ዓመታት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሶማሊያ ሕዝብ ጎን ተለይቶ አያውቅም።

በፊት 'AMISOM' አሁን ደግሞ 'ATMIS' እየተባለ በሚጠራው የአፍሪካ ኅብረት የሶማሊያ ሰላም ማስከበር ተልዕኮ በኩል ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሰላም ጉልህ አስተዋጽኦ ስታደርግ ቆይታለች። በዚህ ተልኮም አብዛኛውን የሶማሊያ መሬት በመሸፈንና ከጥቃት በመከላከል የሶማሊያ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፤ የሶማሊያ መንግስትም ተረጋግቶ መንግስታዊ ስራዎችን እንዲያከናውን በማድረግ ላይ ይገኛል።

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት 60 በመቶ የሚሆነውን የሶማሊያ ክፍል የሚጠብቀውና ከአልሻባብ ጥቃት የሚከላከለው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ነው። ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጠንካራ መንግሥት እንዲፈጠር መስዋዕትነት ስትከፍል ቆይታለች። አልሻባብ የሁለቱም የጋራ ጠላት መሆኑ ደግሞ ሁለቱ ሀገራት በጋራ እንዲቆሙ የሚያስገድድ ነው።

የኢትዮጵያን የሶማሊያ ግንኙነት ከዚህም በላይ ነው። የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች በሁለት አገሮች የሚኖሩ አንድ ሕዝቦች ናቸው። ዕጣ ፈንታቸው የተሳሰረ ነው። ወደ 16 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሶማሊያ እ.ኤ.አ. በ2020 ወደ 294 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ሸቀጣ ሸቀጥ ከኢትዮጵያ አስገብታለች። የንግድ ልውውጡም እያደገ እንደሚሄድ ይታመናል።

ሆኖም አሁን ያለው የሶማሊያ መንግስት ይህን ሁሉ የተመለከተ አይመስልም። የኢትዮጵያ መንግስት ወደብና የባህር በር ለኢትጵያ ወሳኝ መሆኑንና የጎረቤት ሀገራትም ኢትጵያን እንዲተባበሯት ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርብም በግልጽ የተቀበለ ሀገር የለም። ስለዚህም በርካታ አማራጮችን በማማተር ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ መንግስት የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ በመንተራስ ከሶማሊ ላንድ ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል። ይህ ስምምነት ደግሞ ከወዲሁ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። በታዋቂ ሰዎች፤ በዲፕሎማቶችና በፖለቲከኞች ጭምር ተገቢነቱ እየተነገረ ነው።

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከስነልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል። የኢትዮጵያን ክብር እና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል። ለበርካታ መሰረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል።

ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታወጣ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል። በዲፕሎማሲ እና በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የኢትጵያ ሚና አሽቆልቁሏል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ መቀጠል ስለማይቻል መንግስት ሰላምን መሰረት ያደረገ አዲስ የባህር በር አማራጭ ይፋ አድርጓል።

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ቀጣናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል። የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊስ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ለጎረቤት ሀገሮች ነው። በተለይም ለቀጠናዊ ግንኙነት የመጀመሪያውን ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖራት ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ልማት በአስተማማኝ መሠረት የሚቆመው የኢትዮጵያ የውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ እንደሆነ እና ይኸው ሰላምና መረጋጋት የሚጸናው ደግሞ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሰላማዊ ግንኙነትን በማዳበርና የአገራቱ ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ ነው። ለዚህም ከጎረቤት አገራት ጋር በወዳጅነት፣ በትብብርና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በሚያመጣ መልኩ የተቃኘ ዲፕሎማሲ ኢትዮጵያ በመከተል ላይ ትገኛለች።

ኢትዮጵያ ለሶማሊ ላንድ የሰጠችውን ዕድል ለሌሎች የሰጠች ቢሆንም የተጠቀመችበት ግን ሶማሊላንድ ብቻ ነች። ዋናዋ ሶማሊያም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ የመሆን ዕድል አላት። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሰሞኑን በፓርላማ ተገኝተው እንዳሉት ‹‹የሶማሊያ መንግስት በአንድ ሰዓት በረራ እና በአንድ ሰዓት ውይይት ይህን ነገር መልክ ማስያዝ ይችላል። በጣም ቀላል ነገር ነው።

ምክንያቱም ከሶማሌ መንግስት ጋር ምንም ጸብ የለንም። የሶማሌ መንግስት የመረጠው ግን እኛን ከማናገር በየሰፈሩ እየዞረ እኛን መክሰስ ነው። ያለኝ ምክር ብር አታብክኑ ነው። በየ ሀገሩ ስንሄድ፤ በጣም ብዙ ወጪ ይወጣል፤ ብር ከምናባክን እሱን ሰብሰብ አድርገን አንድ ኪሎ ሜትር ዎክ ዌይ ብንሰራበት፤ አንድ ትምህርት ቤት መቋዲሾ ብንሰራበት ሕዝብ ይጠቅማል።

እኛን ለመክሰስ ሀገር ለሀገር መሄድ አያስፈልግም። አዲስ አበባ መምጣት ይቻላል። ለመነጋገር ዝግጁ ነን። ሶማሊያ እንድትጎዳ፤ እንድትፈራርስም፤ እንድትበተንም የሚፈልግ መንግስት አይደለም። ቢሆን ልጆቹን ልኮ አይሞቱም። የኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄ የባህር በር ጥያቄ ነው። ይህ ህጋዊ ጥያቄ ነው። ይህን በሰላማዊ እና በንግግር መልኩ እንደማገኛውም /ኮሚዲቲ/ ሸቀጥ ለመቀበል ኢትዮጵያ ዝግጁ ነች።

ለምሳሌ ወይ ሶማሌ፤ ወይ ጅቡቴ ወይም ሌሎቹ፤ የባህር በር አላቸው፤ ግን እንደ ኢትዮጵያ ሊያመርቱ አይችሉም። እኛ የተሻለ መሬት አለን፤ የተሻለ ውሀ አለን፤ ኢነርጂ ምግብም፤ ከኛ አቦካዶ ከእርነሱ፣ ከእነሱ ውሀውን ብንጋራ ምንም ችግር የለውም፤ ንግድ ነው። ተጠቅመው፣ ተጠቅመን፤ አድገው አድገን፣ ተባብረን አብረን ብንሄድ ለአካባቢው ለልጆቻችንም ጠቃሚ ነው። እናንተ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አታንሱ ቢባል ግን፤ ጥያቄ አታንሱ ብለህ የምታፍነው ጉዳይ አይደለም፤ እውነት እስከሆነ ድረስ ጊዜውን ጠብቆ ይወጣል።›› ሲሉ መልዕክት ማስተላለፋቸው የሚታወስ ነው።

ስለዚህም በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን ሕዝብ በ2050 አካባቢ ደግሞ በዕጥፍ የሚያድግ ሕዝብ ተይዞ ‹‹ስለቀይ ባህር እና ስለ ወደብ አታንሳ፤ ዝም ብለህ ተቀመጥ›› የሚል አፋኝ አመለካከት ሊኖር አይገባም። የሶማሊያ መንግስት ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር የተፈራረመችውን የመግባቢያ ሰነድ ማክበር አሊያም ደግሞ የራሷን የባሕር በርና የወደብ አማራጮች ማክበር ይገባታል። ከሁለቱ ውጭ መሆን ግን በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን የሚቀበሉት አይደለም።

ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባሕር በር አላት። ግን ይህ ሁሉ ኪሎ ሜትር ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም። ስለዚህም ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች ወደብ ከኢትዮጵያ ጋር ማልማት ትችላለች። ወይንም ደግሞ ለም መሬት ወስዳ በምትኩ ወደብ ልታቀርብልን ትችላለች። ብቻ አማራጩ ብዙ ነው።

ዘይላ ሶማሊያ እንደሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነው። ከዛግዌ መንግስት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች። ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው። ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም። ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበት እና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ።

ከዚህ በተረፈ ግን የኢትዮጵያን ፍላጎት አፍኖ አሸናፊ መሆን አይቻልም። ለሶማሊያ ሕዝብ በርካታ ውለታ ለዋለችው ኢትዮጵያ በየስፍራው እየዞሩ ስም ማጥፋትና በኢትዮጵያን ላይ ሀገራት የተሳሳተ አቋም እንዲይዙ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት የኢትዮጵያን ውለታ የዘነጋ ነው። ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በፓርላማ ተገኝተው እንደተናገሩት የሶማሊያን ሕዝብ ለመታደግ ሲባል ኢትዮጵያ በርካታ ወታደሮቿን አጥታለች።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት የሶማሌ ሕዝብ፤ የሶማሌ ጎሳዎች በአብዛኛው በእኛ ውስጥ ስላሉ ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ወንድሞቻችን ናቸው። ለሶማሊያ ሰላም ሞተናል፤ ለሶማሊያ አንድነት ሞተናል። ለሶማሊያ ያለንን ክብር፤ ብልጽግና ከማንም መንግስታት በላይ አሳይተናል።

ሶማሌን እንደ ኢትዮጵያዊ ቆጥረን የደገፍነው እኛ ነን። በሶማሌ አንድነት የኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄ የለውም። በእኛ እና በሶማሌ ላንድ መካከል የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት ለሁሉም ጎረቤቶቻችን ያቀረብነው ጥያቄ፤ ሁሉን ጠይቀን ምላሽ ስናጣ ከመለሰልን አካል ጋር ተፈራረምን እንጂ፤ ከሶማሊያ አንድነት ጋር የተያያዘ ጥያቄ አይደለለም ብለዋል።

> **የኢትዮጵያን የሶማሊያ ግንኙነት ከዚህም በላይ ነው። የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች በሁለት አገሮች የሚኖሩ አንድ ሕዝቦች ናቸው። ዕጣ ፈንታቸው የተሳሰረ ነው። ወደ 16 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሶማሊያ እ.ኤ.አ. በ2020 ወደ 294 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ሸቀጣ ሸቀጥ ከኢትዮጵያ አስገብታለች**

ሆኖም የሶማሊያ መንግስት ይህን ሁሉ በመዘንጋት ወይም ለኢትዮጵያ ውለታ ፊቱን በማዞር ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር አብሮ እየሰራ ነው። ከዚያም አልፎ ሰማሊያ ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል እንዲወጣ ጥያቄ አቅርቧል። ይህ ደግሞ አልሸባብ እንደገና እንዲያንሰራራ እና የሶማሊያ ህዝብ ዳግም ለስቃይ እንዲዳረግ መፍቀድ ነው። ከዚህም አልፎ የምሰራቅ አፍሪካ ቀጣና የአሸባሪዎች መናኸሪያ እንዲሆን በማድረግ የበለጠ የግጭትና የጦርነት ቀጣና እንዲሆን በር የሚከፍት ነው።

የሶማሊያ መንግስት ይህንን ባስታወቀ በጥቂት ቀናት ውስጥ፤ በሞቃዲሾ አካባቢ አምስት የሚሆኑ ወታደሮቹ ተገድለውበታል፤ በርካቶች ቆስለዋል። ስለዚህም የኢትዮጵያ ወታደሮች በሶማሊያ ውስጥ መቆየታቸው የሶማሊያን ሰላምና ጸጥታ አስተማማኝ ከማድረጉም ባሻገር ተሰማርቶ ለሚገኘው የሰላም አስከባሪ ኃይል ትልቅ አቅም የሚሆነው ነው።

ባለፉት 15 ዓመታት እንደታየውም የሶማሊያን ሰላምና ጸጥታ የማስከበር አቅም ያለው የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይል ብቻ ነው። የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይል በሶማሊያ ተልዕኮ ወስዶ ከተሰማራ በኋላ አሸባሪው አልሸባብ ክፉኛ ከመዳከሙም በላይ በአዲስ አበባ በተካሄዱ ተደጋጋሚ ውይይቶች ሶማሊያ አዲስ የሆነ መንግስት እንድትመሰርት አስችሏታል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይል 60 በመቶ የሚሆነውን የሶማሊያን ክፍል ከአልሻባብ ጠብቆ መንግስቷም የተሻለ መረጋጋት እንዲኖረው አስችሎ ቆይቷል።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2008 የሶማሊያ መንግስት ሲቋቋም ቀድማ ኤምባሲ የከፈተችና ዕውቅና የሰጠችው ኢትዮጵያ ናት። በተለያዩ ጊዜያትም በሶማሊያ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የሶማሊያ ሕዝብን በሯን ከፍታ የምትቀበለው ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ታዲያ ይህንን ሁሉ ውለታ ለምትውለው ኢትዮጵያ የሶማሊያ መንግስት በተቃራኒው እየሰራ ያለው ኢትዮጵያን የማጠልሸት ዘመቻ እንቆቅልሽ ሆኖ ዘልቋል።

# የሕይወት ገጽታ

# ከመንግሥት ሠራተኛነት እስከ ኢንቨስተርነት

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

### ቲቶን እንደተረዳሁት

ቲቶ ሐዋርያት ይባላል፤ ጋምቤላ ክልል፣ ማጃንግ ዞን፣ ጎደሬ ያበቀለችው ቁመተ መለሎ ጎልማሳ ነው። ይህ ሰው የባሮ ዳር ፈርጥ፤ የጋምቤላ ከተማ ተምሳሌት ነው። በተምሳሌትነቱም በርካቶች ያውቁታል። በአካባቢው በሚገኘው በማርና በወተት ተቀማጥሎ ያደገ ስለመሆኑ ተክለ ቁመናው በግልፅ ያሳብቃል፤ ንግግሩ ደግሞ ሩቅ አሳቢ ስለመሆኑ ይመሰክራል።

በነበረን አጭር ቆይታ ትህትናው እና ተግባቢነቱ ረጅም መንገድ ለመጓዝ ያሰበ፤ ሩቅ የተለመ ስለመሆኑ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ቲቶ፣ ሥራው ማር-ንግግሩም ማር ነው። ስለሚናገረው ይጠነቀቃል፤ ማር ይበላል፤ እንግዳ ወደ ቤቱ ሲሄድ ማር ያቀርባል። አማርኛ ይቀኛል፤ የማጃንግ ቋንቋ አፍ መፍቻው ነው፤ በአፋን ኦሮሞ ይግባባል፤ ከፍኛ ቋንቋም እንዲሁም የራሱ ነው። እንግሊዘኛን በሥራ እና በትምህርት አግኝቶታል። የቋንቋ እና ተግባቦት ሃብታም ነው።

### የቲቶ መንደር

የቲቶ መንደር ይለያል። ተፈጥሮ ለእርሱ ሰፈር ያደላች ይመስላል። ዞኑ ሙሉ በሙሉ ጫካ ነው። እልፍ ሲሉ ውሃ ነው፤ እንደገና እልፍ ሲባል ደን፣ ውሃ፣ ፍራፍሬ፣ ንብ ነው፤ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ከመሆኑ የተነሳ አካባቢውን ዝቅ ብሎ ለተመለከተ ሰው አረንጓዴ ስጋጃ የለበሰ ይመስላል። ቀና ሲሉ ደግሞ እርስ በእርስ ተቆልፈው ሰማይን የጋረዱ ዛፎች ቅርንጫፋቸውን አጣምረው የጥዋት ጀንበር በጭላንጭል ብቻ ምድሪቱን እንድትሞቅ አስገድደዋል። ተፈጥሮ ተፈጥሮን ሲገድብ የጫካው እና የጥዋት ጀንበር አሙቂኝ አላሞቅም ግብግብ በማጃንግ ምድር አንዱ ለአንዱ ምስክር ናቸው።

በጫካው ያሉ ጦጣዎች በነፃነት ከአንዱ ዛፍ ወደሌላኛው ዛፉ ይንጠላጠላሉ። ማጃንግ ዞን በተባበሩት መንግስታት የትምህርትና ባህልና ቅርስ ድርጅት (ዩኒስኮ) የተመዘገበ ደን ያለበት ሲሆን፣ በዚህ ውስጥም በርካታ አዕዋፍ እና የዱር እንስሳ ይገኙበታል። በጫካው ውስጥ በቅርብ ርቀቱ ባህላዊ ቀፎዎች ተሰቅለዋል። በእርግጥ በማጃንግ ብሄረሰብ ዞን ደን እና ሰው በእጅጉ ተስማምቶ የሚኖርበት፤ አንዱ ለአንዱ የሚጨነቅበት ነው ቢባል ማጋነን አይደለም።

በቲቶ መንደር በርካታ ቀፎች ተሰቅለዋል። የአካባቢው ነዋሪም የቲቶ ቀፎ እያለ ይጠራቸዋል። ይህ ሰው በተወለደበት አካባቢው የሚወደድ ነው፤ ብዙ በጎ ተፅዕኖም የፈጠረ እና የእርሱን እግር ተከትለው ወደተሻለ ሕይወትም እያመሩ ያሉ ወጣቶች አሉ። እናም ቲቶ በዚህ መንደር የበጎ ሰዎች ተምሳሌት ነው።

### ብቸኛው ልጅ

ለእናቱ ብቸኛ ልጅ ነው። በአጋጣሚ ደግሞ የትዳር አጋራቸውም ለእናታቸው ብቸኛ ልጅ ናቸው። ሁለቱም ለእናታቸው ብቸኛ ልጅ መሆናቸውን ያወቁት ግን በትዳር አብሮ መኖር ከጀመሩ ዓመታት በኋላ ከዕለታት በአንድ ቀን በተነሳ ጨዋታ ነው። በአባታቸው በኩል ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ በርከት ያሉ እህቶች እና ወንድሞች አሏቸው - አቶ ቲቶ እና ባለቤታቸው።

### ትምህርት እና ልጅነት

ቲቶ እናት አንድ ልጃቸውን ከአጠገባቸው እንዲርቅ ባይፈልጉም ከቀለም ትምህርት ግን ማናጠብ አልፈለጉም። ይልቁንም ተምሮ በሀገሬው ዘንድ የተከበረ ይሆን ዘንድ የዘወትር ምኞታቸው ነው። አንድ ልጃቸውን በእጅጉ ይሳሱለታል። በአካባቢው ሸክላ ሥራ ተለመደ ነው። እናም አንዳንድ ጊዜ ልጃቸው ብቸኛ መሆኑን፤ ሲሰሩ ‹‹አንተ ሸክላ ብትሆን እዚሁ አቡክቼ እዚሁ ሰርቼ ብዙ አደርግህ ነበር›› እያሉም ይቀልዱበታል። ግን ደግሞ ገና በማለዳቸው ሲመርቁት፤ “አንተ አንድ ሆነህ እንደ ሺህ ታፈራለህ፤ ዘር ይለመልማል” እያሉ ነው። ቲቶም ደስ ይለዋል፤ ቲቶ ያደገው ይህን በአእምሮ እያሰላሰለ እና ደጋግሞ እያሰበም ነው። በተቻለ መጠን ለተወለደበት አካባቢ አርዓያ ለመሆንም ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም፤ ያልቧጠጠው ተራራ አልነበረም። ታዲያ ያሰበው ነገር እንዲሁ መና አልቀረም፤ የእናቱ ምኞትምና ምርቃትም አልባከነም። በአካባቢው በርካቶች ትምህርት ላይ ብዙ ባያተኩሩም እርሱ ግን ትምህርቱን በተቻለ መጠን ገፍቶበታል።

ቲቶ የትምህርትን ጥቅም ብዙ ባያውቅም ገና በልጅነቱ መማር ይፈልግ ነበር። በተለይ ደግሞ ወላጅ እናቱ ለትምህርት በጣም ጉጉት ነበራቸው። በልጅነቱም መርቀው ወደ ትምህርት ቤት ሸኙት። እርሱም ቦርሳውን አንግቶ ከመንደሩ ጥቂት ተማሪዎች ጋር ወደ አስኳላ ትምህርት አቀና። ጎሸኔ፣ ገለሻ እና አካሺ በሚባሉ ትምህርት ቤቶች እየተዘዋወሩ ከአንደኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋል።

በ1990 ዓ.ም ደግሞ በወቅቱ ለታዳጊ ክልሎች በሚሰጠው የትምህርት ዕድል መሠረት ወደ አዲስ አበባ አምርቶ ከ8ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የአዳሪ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ተከታተለ። ከዚያም ወደ ጋምቤላ ክልል በመመለስ ኮሌጅ ሰልጥኖ አጠናቀቀ። የኮሌጅ ምረቃ ከተከናወነ በኋላ ያለአንዳች ቆይታ ሥራ ላይ ተመደበ፤ መምህርም ሆነ። ከተማሪነት ወደ አስተማሪነት በመሸጋገር አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ጀመረ።

### ሥራ


ፈርጣማው ወጣት አሁን ከትምህርት ዓለም ወደ ሌላኛው የሕይወት ምዕራፍ ተሸጋገሩ። ወደ ተወለዱበት ጎደሬ ወረዳ ተመልሰው በመምህርነት ለአንድ ዓመት አገለገሉ። ወርሃዊ ደመወዛቸውም 450 ብር ተወሰነላቸው። ታዲያ ታታሪ እና ጎበዝ ሰራተኛ ስለሆኑ በርካቶች ትኩረት ጣሉባቸው። ከወረዳ እስከ ዞን ብሎም ክልል ድረስ በአጭር ጊዜ ለመዝለቅ የሚያስችል ብቃት አሳዩ። ከአንድ ዓመት የሥራ ቆይታ በኋላ ማለትም በ1995 ዓ.ም በጋምቤላ ክልል ሹመት ተሰጣቸው። ከዚህ ቀን ጀምሮ በክልሉ የተለያዩ ቢሮዎች እና ጽህፈት ቤቶች በኃላፊነት አገልግለዋል።

ከ21 ዓመት የሥራ ዘመናቸው 20 ዓመታት ሙሉ የቆዩት በአመራርነት ላይ ነው። ከእነዚህም መካከል የፓርቲ ጽህፈት ቤት፣ ንግድ ቢሮ፣ ገቢዎች ቢሮ፣ በሕዝብ ተሳትፎ፣ ኮሌጅ ዲን፣ የክልሉ ዋና አፈ ጉባኤ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ውስጥ ቋሚ ኮሚቴ አባል ናቸው። እነዚህ የስልጣን እርከኖችን በአግባቡ ተጠቅመዋል፤ ሕዝብ የጣለባቸውን ኃላፊነትም በአግባቡ ተወጥተዋል።

### የሥራ መልቀቂያ

አቶ ቲቶ በአሁኑ ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ውስጥ ቋሚ ኮሚቴ አባል ቢሆኑም ሥራ መልቀቂያ ጠይቀዋል፤ ምክንያታቸው ደግሞ ኃላፊነት በቃኝ የራሴን ሥራ ልጀምር የሚል ነው። እንደ እርሳቸው አባባል፤ ‹‹እኔ በግል ጠንክሬ ከሠራሁ ራሴንም ሀገሬንም እለውጣለሁ ብዬ አምናለሁ፤ በተለይም እንደ ሀገር የተጀመረው የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴ በርካቶችን እያነቃቃ እና ለውጥም እየተመዘገበ በመሆኑ ይህ መልካም አጋጣሚ ነው። እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ የግብርና ሥራን በጣም የምወድ በመሆኑ ወደምወደው ግብርና ለመግባት ወስኛለሁ። ›› ይላሉ።

“እኔ ይህን ውሳኔ ስወስን ወይንም ወደግል ሥራዬ ስገባ የመንግስት ሥራ ይበደላል። በመሆኑም ሙሉ ለሙሉ ወደ ግል ሥራ መዞር ስላለብኝ የመንግስት ሥራ ማቆም እንዳለብኝ ለራሴ ነገርኩት። በተለይም ሕዝባዊ ኃላፊነት ተሸክሞ በሙሉ ልብና ጊዜ በሥራው ላይ አለመገኘት ሕዝብን መበደል መስሎ እየተሰማኝ መጣ። በዚህ ሁኔታም መቀጠል ለእኔም፣ ለማኅበረሰቡም ብሎም ለሀገሬ የሚጠቅም አይደለም። ሥለዚህ ከሁለት አንዱን መምረጥ ግድ ይለኝ ስለነበር የሥራ መልቀቂያ አስገባሁ። ” ይላሉ-ቲቶ ሐዋርያት።



ፎቶ- ሀዲስ አብርሃ፣

‹‹እኔ በግል ጠንክሬ ከሠራሁ ራሴንም ሀገሬንም እለውጣለሁ ብዬ አምናለሁ፤ በተለይም እንደ ሀገር የተጀመረው የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴ በርካቶችን እያነቃቃ እና ለውጥም እየተመዘገበ በመሆኑ ይህ መልካም አጋጣሚ ነው። እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ የግብርና ሥራን በጣም የምወድ በመሆኑ ወደምወደው ግብርና ለመግባት ወስኛለሁ››

### ንብ ማነብ

ሰውየው ከልጅነታቸው ጀምሮ የግብርና ፍቅር በአዕምሯቸው ውስጥ አለ። ይሁንና በመንግስት የስራ ኃላፊነት ላይ በመጠመዳቸው ሙሉ ለሙሉ ብለው አልገቡበትም። ግን ከአራት ዓመት በፊት ንብ ማነብ እና ማር ማምረቱን በሰፊው ተያያዙት፡ በጥቂት ቀፎ የተጀመረው ሥራ እያደገ በመምጣቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቀፎዎችን ማስቆጠሩ ቻሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን የቲቶ ቀፎ ያለበት ሁሉ የሰፈሩ መለያ እስከመሆንም ደረሰ። ሰዎች በዚያ መንደር ሲያልፉም በርከት ብለው ከጫካው ውስጥ የተደረደሩ ቀፎዎችን ከተመለከቱ የቲቶ ንብረት ስለመሆኑ ይናገራሉ። ቲቶ ሐዋሪያትና ቤተሰቡ ከባህላዊ ቀፎ ወደ ዘመናዊ ቀፎ በመሸጋገር ሥራውን አዘመኑት። ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ደግሞ ንብ ከማነብና ማር ከማምረት ወደ ሌላ የግብርና ዘርፍ ተሸጋግረዋል። ሙዝ ላይ በሰፊው መሥራት ጀመሩ። በአሁን ወቅት ሦስት ሄክታር መሬት የሚጠጋ የሙዝ እርሻ አላቸው።

### ሽግግር ወደ አረንጓዴው ወርቅ

የጀመርኩት አንዱ የሥራ ዘርፍ ብቻ ይበቃኛል ብለው የማይቀመጡት አቶ ቲቶ፣ ከአንዱ ስራ ወደ ሌላ ስራ በፍጥነት እየተሸጋገሩ ነው። ከንብ ማነብ ወደ ሙዝ እርሻ መሰስ ብለው ገብተዋል። ይህ አልበቃኝም ብለው አንገታቸውን በረጅሙ አስግገውና የሀገሪቱ ቀዳሚዎቹ የገቢ ምንጭ የሆነው አረንጓዴ ወርቅ ለማምረት በማለም ወደ ቡና እርሻ አማትረዋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሙሉ አቅም ወደ ቡና እርሻ ለመግባት እየተንደረደሩ ነው። የቡና እርሻ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል። ለዚህም የሚሆን ተስማሚ ቦታ ለማግኘት ለጎደሬ ወረዳ ዞን እና ክልል በየደረጃ ለሚመለከታቸው አካላት አሳውቀው የኢንቨስመንት ይሁንታ አግኝተው አሁን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ከመንግሥት ሠራተኛነት ...

ከገጽ 6 የዞረ



> “እኔ 30 ቀን ሰርቼ አንድ ቀን ደመወዝ ከምቀበል፤ አንድ ቀን ሰርቼ 30 ቀን ደመወዝ የምቀበልበትን ዕድል መፍጠር እፈልጋለሁ። መሻቴ መቀጠር ሳይሆን ለብዙዎች የሥራ እድል መፍጠር ነው። ለአካባቢው ብሎም ለክልሉ በመልካም አርዓያነት መጠቀስን እሻለሁ። ”

### ሰዎች ደነገጡ

አቶ ቲቶ ሐዋርያት፣ ሹመት አልፈልግም ብለው ወደ ግል ሥራ ሲገቡ ያመነ የለም፤ ሰዎችም ደንግጠዋል። ‹‹ብዙ ሰዎች ደንግጠዋል። እውነት አልመሰላቸውም። አልተለመደም። በእኛ አካባቢ ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚጣሉት እና እንደ ክልልም የግጭት መንስኤ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ የወንበር ሽሚያ ጉዳይ ነው። በበርካቶች ዘንድ ስልጣን የመያዝ ፍላጎት አለ። ስልጣን ለመያዝ አንዱን በሌላ ላይ ማነሳሳትና ማደራጀት አለ›› ይላሉ ያለውን ሽኩቻ ሲገልፁ። በመሆኑም እኔ በተለየ መልኩ ሕይወት ምቾት የሚሰጠው በስልጣን ላይ ሳይሆን በሌላኛው ገጽታ መሆኑን ለማሳየት ስል ብሎም የምወደውን ሥራ ለመሥራት በማሰብ ማመልከቻ አስገባሁ ባይ ናቸው። የጀመሩት ሥራ አዳካሚ ቢሆንም በብዙ እጥፍ አትራፊ እንደሚሆኑም አይጠራጠሩም። ከገቢ አኳያም በመንግስት ሥራ ላይ ከሚያገኙት የሰማይ እና ምድር ያህል ልዩነት እንዳለው ይናገራሉ። በእርግጥ እኔ ኃላፊነት ትቼ ወደዚህ ስራ ስገባ በርካቶች ዘንድ አግራሞት ተፈጥሯል፤ ተገርመዋል፤ ለምን? ብለው ጠይቀዋልም። እኔ ደግሞ የተገነዘብኩት ነገር አለ። የምለፋው ዕድሜ ልኬን ሳይሆን በጣም ጥቂት ዓመታትን ነው። በጥቂት ዓመት ውስጥ በገንዘብ ደረጃም ሐብታም መሆን እንደሚቻል አይቻለሁ። ይህን ውሳኔ ስወስን ደጋግሜ አስቤ ነው ይላሉ።

### ቤተሰብ

እኚህ ሰው በትዳራቸው ስኬታማ ከሚባሉት መካከል ናቸው። ከባለቤታቸው ጋር ከተጋቡ 26 ዓመታት ተቆጥረዋል። በጋ ሙቀቱን፤ ክረምት ደግሞ ብርዱን፤ በችግር ጊዜ ውጣ ውረዱን አብረው ተጋፍጠዋል። አምስት የአብራካቸው ክፋዮች አሏቸው፤ አንዲት ሴት እና አራት ወንዶች ናቸው። ልጆቻቸው በሙሉ ትምህርት ላይ ናቸው።

የቲቶ ትዳር አጋር ጠንቃቃ ወይዘሮ ናቸው። ወይዘሮዋ፣ የመንግስት ተቀጣሪ ቢሆኑም፤ ባለቤታቸውን በማገዝ ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን የንብ ማነብ ሆነ እርሻው የበለጠ እንዲስፋፋ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፤ ይመካከራሉ፤ በበጎ አንደበት ይነጋገራሉ። ስለነጋቸው ማማር አብረው ይወጥናሉ። ከዓይን ጥቅሻ በፈጠነ ሁኔታ ይናበባሉ፤ ይግባባሉ። ልጆቻቸውም ቢሆኑ አባታቸው ሥራ መልቀቂያ ማስገባቱን ሲረዱ ጠንክረን እንሰራለን ብለው አበረታትተዋል።

“እኔ 30 ቀን ሰርቼ አንድ ቀን ደመወዝ ከምቀበል፤ አንድ ቀን ሰርቼ 30 ቀን ደመወዝ የምቀበልበትን ዕድል መፍጠር እፈልጋለሁ። መሻቴ መቀጠር ሳይሆን ለብዙዎች የሥራ እድል መፍጠር ነው። ለአካባቢው ብሎም ለክልሉ በመልካም አርዓያነት መጠቀስን እሻለሁ። ” ይላሉ።

### እናቴ ብትኖር...

አባቴ ከሌላ የወለዳቸው ሁለት ወንድሞች ከእኔ ጋር ይኖራሉ። ማር እያስተዋወቁና እና እየሸጡ ደመወዝ ይከፈላቸዋል። በአሁኑ ወቅት በዓመት ሁለት ሺ ኪሎ ግራም ማር እያመረትኩ ነው። በቅርቡ ይህን አምስት ሺ ኪሎ ግራም አደርሳለሁ። ሙዝ እና የቡና እርሻውም እያደገ እና እየሰፋ ሲመጣ በርካቶች ሥራ ዕድል ተጠቃሚ ይሆናሉ።

አሁን ላይ ግን አንድ ነገር ይቆጨኛል። በዚያን ጊዜ የአካባቢያችን ሰዎች ለትምህርት ብዙም ትኩረት በማይሰጡበት ወቅት እናቴ ብቸኛ ልጇን ወደ ትምህርት ቤት ሂድ ብላ የመከረችበትና የዕውቀት ጥማቷን የገለፀችበት ብሎም ስስቷን ያሳየችበት የሸከላው አባባል በአዕምሮዬ ይመላለሳል። ዛሬ ሁሉን ነገር የኋሊት አስባለሁ። እናቴ ብትኖር ብዬ እመኛለሁ። ያለፍኩበትን ሁሉን ነገር ታውቃለች፤ ለእኔ ብዙ ተመኝታለች፤ በብዙ ደክማለች፤ አሁን የደረስኩበትን ግን ሳታይ ከዚህ ዓለም አልፋለች። የልፋቷን ፍሬ ብትመለከተው ብዬ አስባለሁ፤ ግን ፈጣሪ አይሳሳትም ብዬ እጽናናለሁ።

### ደን እና ማዝንግ

ደን እና ማዣንግ የማይለያዩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽዎች ናቸው። ደን ጠፋ ማለት ማጃንግ ጠፋ ማለት ነው። ደን ለእኔ ብሄረሰብ፣ ዞን፣ ሕይወትም ጭምር ነው። ማንነታችን የተመሰረተው እዚህ ላይ ነው። እኔም ይህ የሕይወታችን መሰረት የሆነው ደን እንዳይነካ ሌት ተቀን አስተምራለሁ፤ ከማህበረሰቡም ጋር በቅርበት እሰራለሁ። እኔም ብቻ ሳልሆን በርካታ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ደን እንዳይመነጠር የአካባቢውን ማህበረሰብ በማሰልጠንና በተለያዩ የስራ ዘርፎች በማሰማራት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነው።

የዞኑም ሆነ የክልሉ መንግስትም በማጃንግ ዞን ያለው ደን እንደተጠበቀ እንዲቀጥል የሚሰሩት ስራ ተስፋ ሰጪ ነው። ማህበረሰቡም ከጥንት ጀምሮ ያዳበረው ደን የመጠበቅ ባህል ከፍ ያለ ነው። ይህ በመሆኑ ማር፣ ውብ ተፈጥሮ እና የተፈጥሮ ፏፏቴ ብሎም በደኑ ውስጥ ያሉ በረከቶች ሁሉም ለዛቸውን ጠብቀው ውበታቸው ፈክቶ ይቀጥላሉ ሲሉ ተስፋቸውን ይገልፃሉ።

### ካፒታላቸው

በጥሬ ገንዘብ ምንም የለኝም ማለት ይቻላል ይላሉ። በጋምቤላ ከተማ እያንዳንዳቸው 400 ካሬ ሜትር ላይ ያረፉ ሁለት ቤቶች በተመሳሳይ ማጃንግ ዞን ሁለት ቤቶች አሏቸው። በጎደሬ ወረዳም በተመሳሳይ ቤቶች አሏቸው። በተወለዱበት ሰፈርም እርሻ እና የገጠር ቤት አላቸው። ከ400 ያላነሰ ቀፎ ብሎም የቡና እና የሙዝ እርሻ አላቸው። እነዚህ ተደምረው በትንሹ ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል አለኝ ይላሉ። ይህ በጥናት እና በትክክለኛ ሂሳብ አያያዝ ላይ ቢመሰረት ከዚህ በላይ ነው። እኔ ምኞቴ ካፒታል መቁጠር ብቻ ሳይሆን የማይሞት ራዕይ መትከል ነው። ከእኔ የተሻሉ ብዙ ሰዎች በአካባቢያችን፣ በዞናችንና በክልላችን እንዲኖሩ ነው። ሥራ ወዳድ ዜጋ ከተፈጠረ እና ጥረት ከታከለ ከካፒታል በላይ ደስታ ይሰጣል ሲሉ ይናገራሉ።

### የደመወዝ ነገር

1994 ዓ.ም የወር ደመወዛቸው 450 ብር ነበር። 20 ዓመት አገልግለው በመጨረሻ የሥራ መልቀቂያ ሲያስገቡ ደመወዛቸው 15 ሺ ብር ነው። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በቀን ከአንድ ሺ 500 እስከ ሁለት ሺ ብር አገኛለሁ። ይህን ሳነፃፅረው ይገርመኛል ይላሉ። ይሁንና ሕዝቤ አምስት ጊዜ መርጦኝ ምክር ቤት አገልግያለሁ። ምንም እንኳን ገንዘብ ባላገኝም ኃላፊነቴን ስለተወጣሁ ደስተኛ ነኝ፤ አልቆጭም። ፈጣሪ ይመስገን፤ ጎደለኝ የምለው የለም። አሁን የ43 ዓመት ጎልማሳ ነኝ። ከመጣሁት ይልቅ የምሄደው መንገድ ሩቅ እንደሆነ ስለሚሰማኝ ብዙ ጊዜ ማባከን አልፈልግም። በዕድሜዬ ብዙ ሮጬ፣ በብዙ ደክሜ ብዙ ሃብት ማፍራትና መለወጥ እፈልጋለሁ። እኔም ብቻ ሳልሆን ሌሎችም የእኔን አርዓያ ተከትለው የተሻለ እንዲሆኑ እጥራለሁ። ይህን የማደርገው ደግሞ አንድ ሰው ለመኖር እንደ ዜጋ አለፍ ሲል ደግሞ ሀገራዊ ኃላፊነቴን ለመወጣት እና ከሐሊና ወቀሳ ለመዳን ነው።

### መልዕክት

ለጋምቤላ ክልል ብሎም ለአጠቃላይ ወጣቶች ምክር አለኝ ይላሉ - አቶ ቲቶ ሐዋርያት። ‹‹ወጣቶች በጊዜያችን እንጠቀም፤ ስራ መናቅ የለብንም፤ የሥራ ትንሽ የለም። አንድ ሰው ሩቅ መሄድ ካሰበ ጉዞው የሚጀመረው በአንዲት እርምጃ ነው። ለአንድ እርምጃም አንድ እግሩን የግድ ማንሳት አለበት›› ይላሉ። ተስፋ መቁረጥ፣ የተሸናፊነት ስሜት በወጣት ልብ ውስጥ መኖር የለበትም።

በከተማችን በርካታ ወጣቶች አልባሌ ቦታ እየዋሉ በመሆኑ ወደ ሥራ ማተኮር አለባቸው። ዓለም የምትቀየረው በሥራ እና በሥራ ፈጣሪ እጆች ነው። ለፈጠራ እና አዳዲስ ሃሳቦች በራችን ዝግ መሆን የለበትም። ሕይወት መስመሯ ብዙ ነው። በሮቿ ብዙ ናቸው። እነዚህን በሮች ማንኳኳት ይገባል። ሁሉም በር ባይከፍት በደንብ ደጋግመን ያንኳኳናቸው በሮች እንደሚከፈቱ እርግጠኛ መሆን አለብን። በመሆኑም ጥረት፣ እውቀትና ጥበብ ይዘን መስራት አለብን። እኔ ይህን ምክር ደጋግሜ መናገር የምፈልገው ለጋምቤላ ከተማ ወጣቶች ነው። በጊዜያችን ሰርተን፣ ለራሳችን ሰርተን፣ ራሳችንን እንጠቀም።

# የቱሪዝም ዘርፉ ስኬታማ አፈፃፀምና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

**ዳግም ከበደ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ በተለይ ደግሞ በመዳረሻ ልማት ከፍተኛ መሻሻል እያሳየች መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ዘርፉ ከአምስቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ እንደ አንዱ ተደርጎ መወሰዱና ይህን ተከትሎም በተለይ በመንግስት የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ለውጤታማ አፈፃፀሙ ምክንያት መሆኑ ይገለጻል።

በቱሪዝም ዘርፍ እንደ በጎ ጅምር ከሚወሰዱ የመዳረሻ ልማት ስራዎች ውስጥ ግንባታቸው ተጠናቆ ለጎብኚዎች ክፍት የተደረጉት በአዲስ አበባ ተገንብተው ወደ ስራ የገቡት የገበታ ለሸገሮቹ የእንጦጦ፣ አንድነትና ወዳጅነት ፓርኮች፤ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት አካላት የሆኑት እንደ ሀላላ ኬላና ጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅ እንዲሁም የወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ እና ሌሎች መሰል የመስህብ ስፍራዎች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

ከመዳረሻ ልማት ባሻገር የቱሪዝም ሚኒስቴርና የሚመለከታቸው የዘርፉ ባለድርሻዎች በማስታወቂያና ገበያ ልማት በኩል የመስህብ ሀብቶቹን ለዓለም ገበያ ለማቅረብ አዳዲስ ስልቶችን በመከተል እየሰሩ መሆናቸው፣ ከእነዚህ የማስታወቂያና የቱሪስት ፍሰትን ከሚጨምሩ የገበያ ልማት ስራዎች ውስጥ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫሎች እንዲሁም ኮንፍረንሶች ላይ መሳተፍ እንዲሁም የቱሪዝም ዲፕሎማሲ ስራዎችን መተግበርም ሌሎች ለአፈጻጸሙ ውጤታማነት አስተዋጽኦ ያደረጉ ምክንያቶች በሚል ሊወሰዱ ይችላሉ።

የቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርቡ ይፋ እንዳደረገው፤ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ተከትሎ የዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ጎብኚዎች ቁጥር እያደገ መጥቷል። ይህ ቁጥር በዓለም አቀፍ ተፅእኖዎችና በአገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች ከሚታየው ግጭት እና አለመረጋጋት አንፃር ተስፋ ሰጪ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎችም ይናገራሉ። በ2016 በጀት ዓመት፣ በአስር ወራት ውስጥ ብቻ 982 ሺህ ዓለም አቀፍ ጎብኚዎች እንዲሁም 37 ሚሊዮን የአገር ውስጥ ቱሪስቶች ልዩ ልዩ የቱሪዝም መስህቦችን እንደጎበኙ የሚኒስቴሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሲሰጡ፣ በ2016 በጀት ዓመት በቱሪዝም ዘርፍ ስኬታማ ውጤቶች መመዝገባቸውን ተናግረዋል። ከእነዚህ ውጤታማ ተግባሮች ውስጥ አንዱ በአዲስ አበባ እየተተገበረ ያለው የኮሪደር ልማት መሆኑ ተመልክቷል። የአገር ውስጥ ቱሪዝም እድገት እያሳየ መምጣቱንም እንደ በጎ ጅምር ጠቅሰውታል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ የኮሪደር ልማቱ የአዲስ አበባን ገፅታ በማራኪ መልኩ ከመቀየሩም ባሻገር ነዋሪዎች መዝናኛና መናፈሻዎችን በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ እያስቻለ ነው። በቀጣይ አምስትና ስድስት ዓመታት ውስጥ መሰል ስራዎች ተጠናክረው ሲቀጥሉ የአገሪቱ ብሎም የከተማዋን አጠቃላይ ገፅታ ሊሻሻል ይችላል።

በኮሪደር ልማቱ፣ በአዲስ አበባ የተገነቡ አዳዲስ የመዳረሻ ልማቶችን ተከትሎም፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ከፍተኛ እድገት ማስመዝገቡን ጠቅሰው፣ በበጀት ዓመቱ ብቻ 37 ሚሊዮን ገደማ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች የመስህብ ስፍራዎቹን እንደጎበኙ ገልፀዋል። የዜጎች የመዝናናት እና አዳዲስ ቦታዎችን የመመልከት ባህላቸው እየጨመረ መምጣቱንም የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚስተዋለው አለመረጋጋት ሲወገድና የተሟላ ሰላም ሲመጣ ከዚህ በበለጠ መልኩ ቱሪዝም በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ጎብኚዎች ትልቅ ገበያ ሊሆን እንደሚችል አመልክተዋል።

መንግስት ሁሉን አቀፍ የቱሪዝም ለውጥ እንዲመዘገብ እየሰራ መሆኑን ተናግረው፣ ተስፋ ሰጪ ጅምሮች መኖራቸውን ገልፀዋል። የተፈጥሮ ቱሪዝምንም ሆነ መሰል መስህቦችን ለመጎብኘት እንዲያስችሉ ተደርገው በአገር ውስጥ መኪኖች መገጣጠማቸው ከእነዚህ ውስጥ አንዱ መሆኑን አመልክተዋል። ይህም መንግስት ባለሀብቶችን ለመደገፍ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተከናውኖ ለስኬት የበቃ መሆኑን ጠቅሰው፣ የመጀመሪያዎቹ ለሳፋሪ ጉብኝት የሚያገለግሉ መኪኖች መመረታቸውንም ገልፀዋል። ይህ ስኬት ሁሉን አቀፍ ለውጥ ለማምጣት እንደሚረዳም አስገንዝበዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በየካቲት 2016 በተካሄደ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የ100 ቀናት ግምገማ ወቅት ለቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ የሳፋሪ ተሽከርካሪዎች እንዲመረቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሰጡትን አቅጣጫ ተከትሎ ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ ለሳፋሪ አገልግሎት ተሽከርካሪነት የተቀየሩ ባለአንድ ጋቢና ፒክ አፕ መኪናዎችን በናሙናነት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስረክቧል። መኪናዎቹን ለሳፋሪ አገልግሎት እንዲመቹ አድርጎ በመለወጥ ሂደት ውስጥ አምራቾች በሀገር ውስጥ በስፋት የመለወጥ ልምድ እና አቅም ለማዳበር እንደቻሉም ተመልክቷል።

ለቱሪዝም እድገት የሚረዱ አዳዲስ ተግባራትን ከመከወን ባሻገር ዓለም አቀፍ ጎብኚዎችን ለመሳብ የሚረዱ የማስተዋወቅ ተግባራት በባለድርሻ አካላት እየተከናወኑ መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ በርካታ መረጃዎችም እየወጡ ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ወደ ኢትዮጵያ በመጋበዝ እንዲሁም የመስህብ ስፍራዎችንና የኢትዮጵያን ገፅታ የሚቀይሩ እውነታዎችን በማስተዋወቅ ዓለም አቀፍ የገበያ ድርሻን ለማስፋት የሚደረገው ጥረት ይገኝበታል። ከሰሞኑም በዚህ ረገድ ስኬታማ ስራዎች መከናወናቸውን የቱሪዝም ሚኒስቴር ያወጣው መረጃ ያመለክታል።

የ2016 በጀት ዓመት የ10 ወራት የማክሮ ኢኮኖሚ የዘርፎች ዋና ዋና አፈፃፀም እና የ2017 የትኩረት አቅጣጫዎችን አስመልክቶ የተደረገውን ውይይት ተከትሎም የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ የቱሪዝም ዘርፉን አፈፃፀም የሚመለከት ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የቱሪዝም ዘርፉ በሁለት ንኡስ ዘርፎች ተከፍሎ ዋና ዋና ስራዎችን እንዲያከናውን እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል። እነዚህም የመዳረሻ ልማት እና የማስተዋወቅና የገበያ ልማት መሆናቸውን ይገልፃሉ።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት ከገበያና ማስተዋወቅ ተግባር አንፃር ሰፋፊ ስራዎች በአገር ውስጥና በውጪ ሀገሮች ተከናውነዋል። በውጪ ከተሰሩት ተግባራት ውስጥ ዓለም አቀፍ የቱሪዝምና ንግድ አውደርእዮች (trade fair) ላይ ለመሳተፍ፣ ዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ለመግባት እድል መክፈት የሚችሉ ቱር ኦፕሬተሮችን ወደ አገር ውስጥ ለማምጣትና የትውውቅ መድረኮችን ለመፍጠር (familiarization trip) ተሰርቷል፤ በዚህም ዓለም አቀፍ ተደራሽነትንና ተቀባይነትን ለማግኘት ጥረት ተደርጓል።

እርምጃውን ተከትሎ በተለይ ወደ ኤዢያ አገራት (በተለይ ቻይና)፣ ወደ መካከለኛው ምስራቅ አገራትና ደቡብ አሜሪካ አገራት በመሄድ የትውውቅና የገፅታ ግንባታን የሚያፋጥኑ መድረኮች መፈጠራቸውን ሚኒስትሯ ጠቅሰዋል። ይህም የዓለም አቀፍ ቱሪስቶችን ቁጥር በመጨመር ረገድ የበኩሉን አስተዋፆ እንደሚያበረክት ይገልፃሉ።

ሚኒስትሯ በሶስተኛው ሩብ ዓመትም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያቀደውን ያህል ዓለም አቀፍ ቱሪስት ወደ አገር ውስጥ መሳብ መቻሉን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ፍላጎት እንዲሁም ካለው አቅም አንፃር ሲታይ በቀጣይ ብዙ ስራዎች እንደሚቀሩ አመላክተዋል። ቀሪ ስራዎችን አስመልክተው ሲያብራሩም በአንዳንድ አገራት ወደ ኢትዮጵያ ጎብኚዎች እንዳይገቡ የሚያደርጓቸው የጉዞ ክልከላዎች መኖራቸውን ጠቁመው፣ ይህንን ገፅታ መቀየር እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል። የጉዞ ክልከላውን አልፈው የመጡ ጎብኚዎች መኖራቸውን አስታውቀው፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ካስቀመጠው እቅድ አንፃር በቂ የቱሪስት ቁጥር ወደ አገር ውስጥ መግባቱን አመልክተዋል።

ከገቢም አንፃር አመርቂ ውጤት መታየቱን የጠቀሱት አምባሳደር ናሲሴ፣ በአገር ውስጥ የጉብኝት ባህል እየዳበረ መምጣቱን፤ በተለይ ወጣቱ የተለያዩ የጉብኝት ጉዞዎችን (የተራራ መውጣት፣ በቡድን ጉዞ ማድረግን የመሳሰሉ) እንደሚያደርግ አንስተዋል። ከዚህ ባሻገር በማይስ (ስብሰባና አውደ ርዕይ) ቱሪዝም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከእቅድ በላይ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን (በጤና፣ በኢንዱስትሪ፣ በማኑፋክቸሪንግና በልዩ ልዩ ዘርፎች ላይ) ያተኮሩ አውደ ርእዮችንና መሰል መድረኮችን ማዘጋጀት መቻሉንም ይገልፃሉ። እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያ በማይስ ቱሪዝም ዘርፍ ስኬታማ ዓመት እንድታሳልፍና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሁነቶች እንዲዘጋጁ ምክንያት መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ሚኒስትሯ በሰጡት ማብራሪያ እንዳስታወቁት፤ በቱሪዝም ዘርፍ ከሚጠበቁ ተግባራት መካከል አንዱ የመዳረሻ ልማት ነው። ከዚህም አኳያ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ወደ ስራ እየገቡ ያሉበት ሁኔታ እንዲሁም የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች ግንባታ መጀመሩ በዘርፉ ከተመዘገቡ ስኬቶች መካከል ናቸው። አፈፃፀማቸውም በመልካም ሁኔታ እየሄደ መሆኑም ሌላው ስኬት ነው።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በበላይነት የሚያከናውናቸው የመዳረሻ ልማት ስራዎች መኖራቸውን የሚገልፁት ሚኒስትሯ፣ ለእዚህም በምሳሌነት የጅማ አባጅፋር ቤተመንግስት የጥገና ስራና አዳዲስ የመዳረሻ ልማት ስራዎች በተፋጠነ ሁኔታ እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። አብዛኛዎቹ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በቀጣዩ ዓመት መጀመሪያ ወራት ላይ ተጠናቅቀው ለአገልግሎት እንደሚበቁ እንደሚጠበቅም ጠቁመዋል።

‹‹ነባር መዳረሻዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እየተሰራ ነው›› የሚሉት ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ፤ በተለይ ከመፀዳጃና ከተለያዩ መሰረተ ልማቶች አንፃር ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ እንደሚሰራ ይናገራሉ። ይህንንም ለመፈፀም የመዳረሻ ልማቶቹ ምን አይነት ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል በሚለው ላይ ደረጃ የማውጣት እና ሰነድ የማዘጋጀት ስራ መዘጋጀቱን ጠቅሰው፣ ከዚህም ባሻገር ወደ ተግባራዊ ስራ ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አመልክተዋል። ክልሎቹም የመዳረሻዎቻቸውን ጥራትና ደረጃ እንዲያሻሽሉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥረት እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

ሚኒስትሯ እንዳብራሩት፤ የአገልግሎት ዘርፉን ጥራት ከማስጠበቅ አንፃር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ ተግባራትን እያከናወነ ነው። ከዚህ አንፃር በሆስፒታሊቲ ዘርፉ የቱሪስት አገልግሎትን የሚያሟሉና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ምደባ ተካሂዷል። ዘንድሮም በድጋሚ የባለኮኮብ ሆቴሎች ምደባ ተካሂዷል፤ በተመሳሳይ በቅርብ ጊዜያትም ሌሎች ተጨማሪ ሆቴሎችን የመመደብ ስራ የሚከናወን ይሆናል።

የሆቴሎች የደረጃ ምደባ የሚያስፈልግበት ዋንኛ ምክንያት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን ነው የሚሉት ሚኒስትሯ፤ ይህንን ተከትሎ ሆቴሎች አሊያም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከሌሎች መሰል ዓለም አቀፍ ሆቴሎችና ተቋማት ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራትና አገልግሎት ደረጃ እንዲኖራቸው እንደሚያግዝ ያስረዳሉ።

እስካሁን ደረጃ ላልወጣላቸው ሬስቶራንቶች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ ሎጆችና ሪዞርቶች ደረጃ የማውጣት ሂደት እየተጠናቀቀ መሆኑን ይናገራሉ። በቅርቡም ልክ እንደሆቴሎቹ ሁሉ እነዚህም የቱሪዝም ዘርፍ የሆስፒታሊቲ አንቀሳቃሾች ደረጃ እንደሚወጣላቸው አስታውቀዋል። ይህም ስራ ከ2017 በጀት ዓመት እቅድ ከቀዳሚ ተግባራት መካከል አንዱ እንደሆነ ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ አጠቃላይ የቱሪዝም ዘርፍ ተግባራት (ከመዳረሻ ልማት፣ ማስተዋወቅ፣ ደረጃ ማውጣት) አንፃር ሰፋፊ ስራዎች መከናወናቸውን ገልፀዋል። እነዚህ ተግባራት ኢትዮጵያ በቱሪዝም መዳረሻነት ከሌሎች አገራት ጋር ተወዳዳሪ እንድትሆን ከፍተኛ አስተዋፆ እንደሚኖራቸውም ጠቁመዋል። በቀጣይ ዓመትም የቱሪስት ፍሰቱ እንደሚጨምር ጠቅሰው፣ እስከ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ እንደሚገቡ ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ስራን አስታክኮም የጊዜያዊነት ትራንዚት የሚያደርጉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተጓዦች የሚኖራቸውን አጭር ሰዓታት ቆይታ አዲስ አበባን የሚጎበኙበት (Stopover tourism) አጋጣሚ የሚጨምርበት፣ አገርም ከዚያ ተጠቃሚ የምትሆንበት ሁኔታ እንዲፈጠር እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ከላይ ከተነሱት ተግባራት በተጨማሪ በዘንድሮው በጀት ዓመት ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት ከመስጠት፤ 60 የሚደርሱ ዓለም አቀፍ አስጎብኚዎች የኢትዮጵያን የመስህብ አቅም ተመልክተው ጎብኚዎችን እንዲያመጡ፣ በቅድሚያም ራሳቸው እንዲጎበኙ ከማድረግ፣ የገበያ ማስተሳሰር ስራን ከማከናወን፤ በውጪ አገራት ውጤታማ የግብይትና የማስተዋወቅ ስራን ከመስራት አንፃር አመርቂ ተግባራት ተከናውነዋል።



የወንጪ ሀይቅ አሁናዊ ገጽታ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ካልተዘመረላቸው አርበኞች

**ዋለልኝ አየለ**

አንዳንድ አርበኞች በኪነ ጥበብ ሥራዎችና በተለያዩ ታሪካዊ ሰነዶች ላይ ስማቸው ተደጋግሞ ይጠቀሳል። በዚህም ምክንያት በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ደምና አጥንታቸውን ለአገራቸው ገብረው ብዙም ሲዘመርላቸው አይሰማም። በእርግጥ የአርበኛ ዓላማውም አገሩን ማዳን እንጂ ዝማሬ እና ዝና ማግኘት አይደለም። ያም ሆኖ ግን አገራችንን ክብሯን አስጠብቀው አስረክበውናልና ሕይወትና ሥራዎቻቸውን እናስታውሳለን።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ109 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 2 ቀን 1907 ዓ.ም የተወለዱትን አርበኛ ኪዳኔ ወልደመድኅን እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እናስታውስ።

ከ13 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 2 ቀን 2003 ዓ.ም ጎረቤታችን ደቡብ ሱዳን 98 በመቶ ድጋፍ ባገኘ ሕዝበ ውሳኔ ከሱዳን ተለይታ ሉዓላዊት አገር ሆነች።

ከ22 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 2 ቀን 1994 ዓ.ም የቀድሞውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተካው የአፍሪካ ሕብረት በደቡብ አፍሪካ ደርባን ተመሰረተ። ስያሜውም ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወደ ዛሬው ስሙ አፍሪካ ሕብረት ተቀየረ። ዋና መቀመጫው ከኢትዮጵያ እንዲነሳ ጥያቄ ያቀረቡ አገራት ቢኖሩም በወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ጠንካራ ትግል ባለበት እንዲጸና ተደርጓል። አቶ መለስ ዜናዊ እንዲህ ብለው ነበር።

«...ኢትዮጵያ ሁልጊዜም ለአፍሪካ ሉዓላዊነትና ነፃነት ቆራጥ ናት!

ማንዴላን ያሰለጠነው ማን ነው? አጼ ኃይለሥላሴ!... ሙጋቤ ሩዲዝምን በሚፋለምበት ጊዜ ማነው የደገፈው? መንግሥቱ! መንግሥቱ በአገር ውስጥ ገዳይ ነው፤ ዳሩ ግን በአፍሪካ ጉዳይ ላይ ልክ እንደ አጼ ኃይለሥላሴ ቆራጥ አቋም ያለው ነው። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ያላት አቋም በመንግሥት መቀያየር ላይ ምንም ለውጥ አይኖረውም! በኃይለሥላሴ፣ በመንግሥቱ፣ በእኛ፣ በአፍካ ጉዳይ ላይ ምንም ለውጥ የለም! ሁሉም አፍሪካዊ ይህን የኢትዮጵያውያን ስሜት ማወቅ አለበት!..»

ከ8 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 4 ቀን 2008 ዓ.ም ነባሩንና ጥንታዊውን የኢትዮጵያ የስዕል ጥበብ ይዘቱን ሳይለቅ ከዘመናዊ የአሳሳል ጥበብ ጋር ለማዋሃድ በተደረጉት ጥረቶች ውስጥ የመሪነት ሚና የነበራቸው ታላቁ ሠዓሊ አለ ፈለገሰላም ኅሩይ አረፉ።

ሐምሌ 5 ቀን 1825 ዓ.ም ኢትዮጵያን ከጥር 1864 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1881 ዓ.ም የመሩት ንጉሰ ነገሥት አጼ ዮሐንስ 4ኛ ተወለዱ። ባለፈው ዓመት በዝርዝር ማስታወሳችን ይታወሳል።

ከ74 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 5 ቀን 1942 ዓ.ም ገጣሚ፣ ፀሐፊ ተውኔት፣ ደራሲ፣ ሃያሲ፣ ተርጓሚ፣ መምህርና የስነ ጽሑፍ ተመራማሪ ደበበ ሰይፉ ተወለደ።


ከ45 ዓመታት በፊት ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሁለተኛው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በወታደራዊው የደርግ መንግሥት ተገደሉ።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን ታሪክ እናልፋለን።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ሊቀ መንበር የነበሩት ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን በዕለተ ዓርብ ሐምሌ 2 ቀን 1907 ዓ.ም ቡልጋ በከሰም ወረዳ፤ የለጥ ቀበሌ፤ ልዩ ስሙ ቡሄ አምባ በሚባለው ሥፍራ፤ ከእናቱ ከወይዘሮ አስካለ ደጀን እና ከአባቱ ከቀኛዝማች ወልደመድኅን አይደረስ ተወለደ። አባቱ ቀኛዝማች ወልደመድኅን በትውልድ አገራቸው በዘመኑ የታወቁ ስመጥር ጠበቃ ነበሩ። ኪዳኔ እስከ 12 ዓመት ዕድሜው ድረስ እዚያው ቡሄ አምባ አካባቢ በአያቱ አቶ ደጀን ደብሩ ቤት ሆኖ የቄስ ትምህርት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተከታትሏል። በመቀጠልም ከወላጆቹ ጋር ሆኖ የአማርኛና የግዕዝ ትምህርቱን አጠናቋል።

ኪዳኔ በ18 ዓመቱ በ1925 ዓ.ም አዲስ አበባ የክብር ዘበኛ ሰራዊት አባል ሆነ። ወዲያው በንጉሡ ነገሥቱ ትዕዛዝ ከ69 አዲስ ወታደሮች ጋር ባሌ ተመድቦ እስከ 1927 ዓ.ም ድረስ በተራ ወታደርነት ከዚያም በሃምሳ አለቃነትና በባሻነት ማዕረግ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት በ1928 ዓ.ም በነደጃዝማች በየነ መርድ መሪነት ከጎባ ወደ ኦጋዴን ዘመተ።

ኪዳኔ ከባላምባራስ አየለ ወልደማርያምና ሌሎች አርበኞች ጋር ሆኖ በዚህ ግንባር በዋቢሸበሌና አካባቢው ለዘጠኝ ወራት ያህል ከጠላት ጋር ሲፋለም ከርሞ ወደ ጎባ ተመለሰ። ከሰኔ 1928 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 1929 ዓ.ም ድረስ ከአርሲ፣ ከሲዳማ፣ ከሐረርና ከኦጋዴን ወደ ጎባ የዘለቀውን የጠላት ጦር ሲዋጉ ከርመው፤ መጨረሻ ላይ ተማም ከሚባለው ሥፍራ ላይ በተካሄደው ጦርነት ማምለጥ በማይቻልበት ሁኔታ ኪዳኔና ሌሎች አርበኞች በጠላት እጅ ወድቀው ተማረኩ። ጠላትም ለአምስት ወራት በጽኑ እሥራት ከያዛቸው በኋላ፤ በጥር ወር 1930 ዓ.ም ከጎባ ወደ ወሊሶ አዛውሮ አሰራቸው።


ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን

ባሻ ኪዳኔም እዚሁ እስር ቤት እያሉ አብረዋቸው ከታሰሩት አርበኞች መካከል በምስጢር 100 ሰዎችን አደራጅተው እዚያ ያለውን የጠላት ጦር ፈጅተው ለመሸፈት ከወሰኑ በኋላ በወቅቱ ከስመ ጥር አርበኞች መካከል አንዱ ወደነበሩት ወደ ባላምባራስ (በኋላ ደጃዝማች) ገረሱ ዱኪ ሰው ለመላክ በመዘጋጀት ላይ ሳሉ አሳሪያቸው የፋሺስት ጦር ነገሩን በመስማቱ እጅግ ጥብቅ የሆነ ክትትል አደረገባቸው። ባሻ ኪዳኔም ይህን ሲገነዘቡ ካደራጇቸው 100 ሰዎች መካከል 55 ወታደር ከነመሳሪያው፤ አራት መትረየስ፤ አስር ሣጥን ጥይት፤ ስድስት ሽጉጥ ከጠላት እጅ ነጥቀው እየተታኮሱ ሲወጡ የጠላት ኃይል ሃያ ወታደርና አንድ መትረየስ ከሁለት ሣጥን ጥይት ጋር ብቻ ገንጥሎ ሲያስቀርባቸው ከተረፈው መሳሪያና ወታደር ጋር ድል አድርገው ሸፈቱ። ወዲያውም ኩሳ ኪዳነምሕረት ከሚባል ሥፍራ ላይ ከደጃዝማች ገረሱ ጋር ተገናኙ።

ባሻ ኪዳኔ ከባላምባራስ ገረሱ ጋር ከተቀላቀሉ በኋላም እስከ ጥቅምት 1931 ዓ.ም ድረስ በደንዲ፤ በሶዶ፤ በበዳቄሮ እና በሌሎች ሥፍራዎች በአርበኝነት ሲዋጉ ቆዩ። በዳቄሮ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ሳሉ ሙሴ ሰባስቲያኖ ካስታኛ (ሙሴ ቀስተኛ) የሚባለው ጣሊያናዊ ከፋሺስት አመራሮች ተልኬያለሁ ብሎ ከሦሥት ባላባቶች ጋር መጣ። አርበኞቹም ይህ ሰው ቀደም ሲል በ1930 ዓ.ም ወደ ራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ሄዶ የጦሩን ኃይል ከተመለከተ በኋላ ብዙ አርበኛ እንዳስገደለ ሰምተው ስለነበር እነሱንም እንደዚሁ ለማስፈጀት እንደመጣ ስለተገነዘቡት ባሻ ኪዳኔ ወልደመድኅን በመውዜር ጠመንጃ ሲመቱት «ኢጣልያ ለዘለዓለም ትኑር! ለኢጣሊያ ስል ሞትኩላት» ብሎ ሲናገር በሽጉጥ ራሱን መትተው ከገደሉት በኋላ የለበሰውን ሙሉ ገበርዲን ልብስና ካፖርት እንዲሁም የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስዕል ያለበትን የብር ሰዓቱንና በቅሎውን ከነኮርቻው ማረኩት። ከሙሴ ካስታኛ ጋር አብረው የመጡት አባላባቶች የሙሴን መገደል ለፋሺስት ጦር መሪዎች አሳወቁ። ከ25 በላይ የጦር አውሮፕላኖች ያሉበት በርካታ የፋሺስት ጦር ወደ በዳቄሮ ዘመተ። አርበኞቹም ለሦስት ቀናት ሙሉ ሲከላከሉ ከቆዩ በኋላ ከሥፍራው ሸሽተው ሶዶ ላይ ለስምንት ቀናት ያህል ተዋጉ።

ባሻ ኪዳኔ በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም አርበኞቻቸውን አስከትለው ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ቡልጋ ገቡ። በዚያም ከፊታውራሪ ኃይለማርያም ማናህሌ እና ከፊታውራሪ ተረፈ ማናህሌ ጋር ተቀላቅለው እስከ መጋቢት 1931 ዓ.ም ድረስ በውሸንግር፤ ጨፌ ዶንሳ ምሽግ፤ ነጭ ድንጋይ ምሽግ፤ ልዝብ ድንጋይ በተባሉ ቦታዎች ላይ ከጠላት ኃይል ጋር ሲዋጉ ከረሙ። በዚህ ወቅት ታመው በነበረበት ጊዜ የፋሺስት ጦር በሦስት አቅጣጫ ከበባቸው። የጠላት ኃይል እጅ እንዲሰጡ ቢጠይቃቸውም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ከህመማቸው ጋር እየታገሉ ከፋሺስት ጋር ተፋለሙ። በወቅቱ ባሻ ኪዳኔ ከፋሺስት ጦር ጋር ያደረጉት ፍልሚያ እጅግ መራራና እልህ አስጨራሽ እንደነበር ስለአርበኞች ታሪክ የተፃፉ መዛግብት ይመሰክራሉ። ከህመም ጋር እየታገሉ ከፋሺስት ጦር ጋር የተፋለሙት ባሻ ኪዳኔ የጠላት ጦር እርሳቸው መሽገውበት የነበረውን ጫካ በእሳት ነበልባል ግራና ቀኙን ሲያቃጥልው እሳቸው በተዓምር ተረፉ። ከሦስት ቀናት በኋላ የጠላት ኃይል አካባቢውን ለቆ ሲሄድ ባሻ ኪዳኔ ህመሙና ድካሙ በርትቶባቸው ስለወደቁ በብዙ ፍለጋ ነበር የተገኙት።

ከዚህ በኋላ ክረምቱን ቡልጋ ውስጥ በነጭ ድንጋይ፣ ፍልፍል አፈር፣ ጦስኝ ምሽግ እና በመስኖ ከነደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በላይነህ፣ ፊታውራሪ በለጠ ሳሴ፣ ፊታውራሪ አጎናፍርና ሌሎችም ስመጥሩ የቡልጋ ልጆች ጋር ሆነው ጠላትን ሲያጠቁና ሲከላከሉ ቆይተው በመስከረም 1932 ዓ.ም በሰገሌ በኩል ተጉዘው ገሊላ ከሚባል ሥፍራ ላይ ከራስ አበበ አረጋይ ጦር ጋር ሲቀላቀሉ ባሻ ኪዳኔ የግራዝማችነት ማዕረግ ተሾሙ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወደ ጎጃምና ወደ ጎንደር እስከዘመቱበት 1933 ዓ.ም ድረስ ከራስ አበበ ጋር ጠላትን በየቦታው ሲዋጉ በአርበኝነት ቆዩ።

ከብዙ ውጊያዎችና ጀብዱዎች በኋላ በየካቲት 1933 ዓ.ም መሶቢት ከሚባለው ቦታ ላይ በመሪነት የጠላትን ጦር ድል አድርገው ወደ ዋናው ሰራዊት ከተቀላቀሉ በኋላ ራስ አበበ የቀኛዝማችነት ማዕረግ ሾሟቸው።

ቀኛዝማች ኪዳኔ ከሌሎች አርበኞች ጋር ሆነው በ1933 ዓ.ም ዳውንት፣ ተንታ እና ደብረታቦር ላይ የሰፈረውን የፋሺስት ጦር እየማረኩ በመስከረም 1934 ዓ.ም ጉማራ ላይ ከፍ ያለ ውጊያ አድርገው ጠላትን ድል አደረጉ። በኅዳር 1934 ዓ.ም ከጎንደር ወደ ቁልቋል በር ላለው ለጠላት ጦር ስንቅና ትጥቅ አቀብሎ ሲመለስ ጥቃት ከፍተውበት ብዙ ባንዳዎችን ገደሉ።

በዚያው በኅዳር ወር 1934 ዓ.ም ጎንደር ከተማ ውስጥ ጄኔራል ናሲ የተባለው የፋሺስት ጦር አዛዥ ከብዙ ሺህ ሰራዊት ጋር አካባቢውን በሽቦ አጥሮ በሽቦው ውስጥና ውጭ ፈንጂና ቦንብ ቀብሮበት ነበር። ቀኛዝማች ኪዳኔ ይህንኑ የተቀበረ ቦንብ እየቆረጡ ሌሊቱን ተጉዘው ምሽጉ ደረሱ። ሲነጋ ተኩስ ተከፈተ። ጠላትም ከከፍተኛ ተራራ ላይ ወደታች ወደነ ቀኛዝማች ኪዳኔ በቦምባርድና ከባድ መትረየስ ሲያጠቃቸው በተራራው ሥር አድርገው ወደ ጎንደር ከተማ የሚወስደው መንገድ ላይ ሲደርሱ ከጎንደር ከተማ የሚመጡ አስመስለው ከኋላው በጨበጣ የእጅ ቦንብ እየጣሉ ብዙ የጠላት ኃይል ደመሰሱ። እንዲሁም መትረየሶችን ማርከውና ምሽጉን አስለቅቀው ከያዙ በኋላ ጄኔራል ናሲ ወዳለበት ወደ ጎንደር መጓዝ ቀጠሉ። ጎንደር ሲገቡም ፋሲል ግንብ ምሽግ ሲደርሱ ምሽጉን ለመድፈር የእጅ ቦንብ ምሽጉ ላይ በብዛት ሲጥሉ ጠላት ተሸንፎ የሰላም ባንዲራ አውለበለበ። ወዲያውኑ 500 የጠላት ወታደሮችን ማረኩ። በከተማው የሚገኙትን የአረብ ተወላጆች ሱቅና ገንዘብ እንዳይዘረፍ በወታደር አስጠብቀው ወደ ቀጣዩ ዘመቻቸው አቀኑ።

ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ራስ ብሩ ወልደብርኤል ከእንግሊዛዊው ሜጀር ጀኔራል ፎክስ ጋር ወደ ጎንደር ገቡ። «ባለህበት እርጋ» ተባለና ሁሉም ተረረጋ። ጀኔራል ናዚ ያለድርድር እጁን ሰጠ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በፋሲለደስ ግንብ ላይ ተውለበለበ። በማግሥቱ ኅዳር 20 ቀን ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ጎንደር ገቡ። የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያ የነበረው ቆይታ ተደመደመ! የጎንደሩ ውጊያና ሽንፈት የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በአፍሪካ ምድር ያካሄደው የመጨረሻው ውጊያና የተከናነበው የመጨረሻው ሽንፈት ሆኖ ተመዘገበ። ቀኛዝማች ኪዳኔ ከአልጋወራሹ ጋር ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት እንዲሄዱ ተደርጎ እዚያው ብዙ ወታደርና መሳሪያ ለመከላከያ ሚኒስቴር አስረከቡ።

በየካቲት 1934 ዓ.ም የፊታውራሪነት ማዕረግ አግኝተው መጀመሪያ በወረዳ አስተዳዳሪነት ከዚያም በ1936 ዓ.ም የየጁ፤ የዋድላ ደላንታ፤ የመቄት፤ የሸደሆና የዳውንት ብሔራዊ ጦር አዛዥና የጠቅላይ ግዛቱ ጦር አማካሪ በመሆን አገለገሉ። ከዚያም እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በወሎና በከፋ ውስጥ በአውራጃ አስተዳዳሪነት ተመድበው ሲያገለግሉ ቆዩ። በዚሁ ወቅት ነው የደጃዝማችነት ማዕረግ የተሰጣቸው።

ደጃዝማች ኪዳኔ ከፋ ውስጥ እንደተሾሙ ከጠቅላይ ገዢው ጋር ባለመስማማታቸው ተሽረው ንጉሠ ነገሥቱ ከስልጣን እስከወረዱበት ጊዜ ድረስ በእስራትና በግዞት እንዲቆዩ ተደርገዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ከስልጣን ከወረዱ በኋላ ደጃዝማች ኪዳኔ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ አገራቸውንና ማኅበሩን ወክለው ሮም ላይ በተካሄደው የዓለም አቀፍ ጸረ ኑክሊየር መሣሪያ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ሲጓዙ ሞስኮ ላይ፣ ጥቅምት 9 ቀን 1972 ዓ.ም አረፉ። ስርዓተ ቀብራቸውም ጥቅምት 15 ቀን 1972 ዓ.ም በአዲስ አበባ መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈፅሟል።

ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን ከአርበኛነታቸው በተጨማሪ በማኅበራዊ ኑሯቸውም ንቁ ተሳታፊ ነበሩ። በ1949 ዓ.ም በትውልድ ስፍራቸው በቡልጋ የየለጥ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን አሰርተዋል። በ1964 ዓ.ም «ከልደት እስከ ሞት» የተሰኘች አጭር ኃይማኖታዊና የፍልስፍና መጽሐፍ አሳትመዋል።

ደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድኅን ከአገር ውስጥ በተጨማሪ በርካታ የውጭ አገራት ሽልማቶችን አግኝተዋል። ከእነዚህም መካከል የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን ባለአምበል፣ የአርበኝነት ሜዳይ ከአራት ዘንባባ ጋር፣ የድል ኮከብ ሜዳይ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ የከፍተኛ ጀብዱ ሜዳይ ከአንድ ዘንባባ ጋር፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ታላቅ መኮንን ከደረት ኮከብ ጋር፣ የአፍሪቃ ኮከብ ሜዳይ (ከእንግሊዝ መንግሥት)፣ የአፍሪካ የድል ሜዳይ (ከእንግሊዝ መንግሥት) እንዲሁም ሦስት ልዩ ልዩ የሶቭየት ኅብረት ኒሻኖች ይጠቀሳሉ።

# የዝነኞች ገጽ

## የደበዘዘች ጽጌረዳ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

የብዙ የሀገራችንን ዝነኞች ጓዳና ጎድጓዳ ተመልክተናል። እንደ ክብር ኒሻን ያንጠለጠሉትን የስኬት ቁልፎቻቸውንም ተመልክተን ከሥራዎቻቸው ጋር ምስጋናንም ቸረናቸዋል። በታሪኮቻቸው ተደንቀናል። ከሕይወታቸው ተምረናል። በደፉት የታላቅነት ዘውድ፣ በደረቡት የዝና ካባ ላይ እጅግ ብዙ ብዙ ተመልክተናል። አንዳንዴ ግን እንዲህም አለ... የኑሮ ውብ ሽክላ ተሰንጥቆ የሞላው የሕይወት ውሀ ሲፈስ... ደግሞ ሲጎድል ሁሉን አጥቶም ባዶ ጥቁር ጋን ታቅፎም ይኖራል።

ከዝነኞቹ መንደር ዝናና ስኬት ብቻ ሳይሆን የፈራረሰ ደሳሳ ጎጆ፣ ከጎጆው በታችም ጥልቅ የሕይወት ጉርጓድ የሚታይበት ሌላ ምዕራፍ አለ። ከዚያ ወድቀው እኛም ደርሰን ያወጣናቸውና ዳግም ያቆምናቸው ምናልባትም አሉ። ግን ደግሞ የወደድናቸውን ያህል ዘንግተናቸው በማጥ ውስጥ ተዘፍቀው ማቅ የለበሱም በርክተዋል። የሙዚቃ ፍቅራችንን አለምልመው፣ ከስራዎቻቸው ጣፋጭ ፍሬን ካቀመሱን የ90ዎቹ ጽጌረዳዎች መሀል አንዷንም እንዲህ ናት... ከስኬቷ ማማ ላይ ብቻም ሳይሆን ከሕይወቷ ደረጃዎች ላይም ወድቃ ውስጧም ጭምር በመሰበሩ ከሁሉም በላይ አሳዛኝ ያደርጋታል። በጸደይ፣ በመስከረም በልምላሜ ፈክታ ከሁሉም አበቦች ውብ መስላ ትታይና ብዙም ሳትርቅ በበጋው ደረቀች። ንፋሱም ቅጠሎቿን አረገፈው። ታዲያ እንዲህ ስትጠወልግ ጽጌረዳ ለምንስ አታሳዝን?... በእንባ ስትታጀብ፣ ስትኮሰምን ጽጌረዳ እንዴትስ አንጀትን አትበላ?...ጊዜ ጌታው እንዳነሳ መልሶ ሲጥል ሕይወትም እንደበረዶ እየቀዘቀዘች አንሸራታ ስትጥል ያሳዝናል። ልብ ይሰብራል። ይኼ ሁሉም የድምጻዊቷ የቤተልሔም መኮንን ጥቁር ጥላ ነው።

ቤተልሔም መኮንን ሲባል ስንቱ እንደሚያስታውሳት አላውቅም። ስሟን የተሸከመውን ሥራዋን ጠርቼ "አነጋግረኝ" ብል ግን ሙዚቃን የሚወዱ ልቦች ሁሉ በደስታ አስታውሰው "አቤት ግሩም ሙዚቃ!" እንደሚሉ ጥርጥር የለውም። ያኔም ቢሆን አሁን በሙዚቃዋ ፍቅር ተለክፈው ለልባቸው ማሰሪያ ያጡ እንደሞሉ ናቸው።

**"መውጫ መግቢያህን ጠብቄ፤**
**አይሀለሁ ከሩቅ ሠርቄ**
**ውስጥ ውስጤን ፍቅር ጨረሰኝ**
**መጥተህ ባክህ አንድ በለኝ...**
**እሂያ! ሂያ ሂያሂ... ሁ... ሁ"**

ይህ ሥራዋ በጊዜው እንደ አንድ ቆንጆ የሙዚቃ ክሊፕ ታይቶ ብቻ የታለፈ አልነበረም። ይህ ሥራ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ክሊፕ ሥራዎች ውስጥ በሁሉም ነገሮች ፈር ቀዳጅ የነበረና ቀድሞ ከነበረው አንድ ከፍታ የተጨመረበት የተለየ ሙዚቃ ስለመሆኑ ብዙዎች ተናግረውለታል። ከቀረጻውና ከሙሉ የሙዚቃው ግብአት ጀምሮ ብዙ አዳዲስ ነገሮች ታይተውበታል። እንዲያውም የዘመናዊው ሙዚቃ አብዮት የፈነዳበት ነው ሲሉ የሚያነሱም እንዲሁ ጥቂት አይደሉም። በሥራው ላይ ከያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት የወጡ ወጣቶችን ጨምሮ ከ23 በላይ ባለሙያዎች ተሳትፈውበታል። ቅንብሩን በተለየ ሁኔታ አሳምሮና ከሽኖ ያዋሀደላት አቀናባሪ ደግሞ ባደግ በቀለ ነበር። ነገር ግን ባደግ ብዙም ሳይቆይ ከሀገር ወጣ። የድምጽዋን ሙያዊ ልኬት ተረድቶ በትክክለኛው ብቃቷ ላይ ያሳረፋት እርሱ ነውና ከሀገር መውጣቱ ለቤተልሔም ጥሩ አጋጣሚ አልነበረም። "አነጋግረኝ" እርሷን ከማሳወቅ አልፎ ተቀጽላ ስሟ ለመሆን የበቃ ቢሆንም ብቸኛው ሥራዋ ግን አይደለም። "ሀብል" የተሰኘ አንድ የአልበም ሥራም አላት። አልበሙን ጨምሮም በድምሩ 15 ያህል ሙዚቃዎችን ሠርታለች። ከ"አነጋግረኝ" በመቀጠልም "የት ነው" የተሰኘው ዜማዋም ተወዳጅነትን ያተረፈላት ሥራ ነው።

**"የት ነው የማገኝህ**
**የት ነው የምፈልግህ**
**ስኔ የተባልክ ሰው**
**ስኔ የተፈጠርከው"**

ዛሬም ድረስ እንደ ዓይን ብሌናችን እያየን ከምንሳሳላቸው የምን ጊዜም እንቁዎች ጋር ልንመለከታት ልትሆን የምትችል ባለተስፋ ወጣት የነበረች ቢሆንም ነገሩ እንዳልታሰበ ሆኖ ቆይቶ ነበር። መቼም ድምጽዋ እንደሆን ለሙዚቃ የሰጠ ነበር። ገና የ17 ዓመት አፍላ ወጣት ሆና በ90ዎቹ አጋማሽ ላይ "አነጋግረኝ"ን ስታወጣ ጆሮ ብቻም ሳይሆን አፍም ጭምር አስከፍታ ነበር። በጣም ተወዳጅ ከመሆኑ የተነሳ የሙዚቃ ቡፌ በተደረደረበት ገበታ ላይ ሁሉ ይገኛል። አሁን ላይ የ90ዎቹ ሙዚቃ ከምን ጊዜም በላይ እጅግ ተወዳጅና ተመራጭ ሆነዋል። ከዘመን ይልቅ እንደ አንድ የሙዚቃ ምድብ እየታዩ ያለ ይመስላል። የወይን ጣዕሙ እየተንጠፈጠፈ የሚወጣው እየቆየ በሄደ ቁጥር እንደ ሆነ ሁሉ የ90ዎቹም ይበልጥ እያስጎመዡ መጥተዋል። ቀዳሚውን ስፍራ ከያዙት መሀከልም ቤተልሔምና ሙዚቃዋ "አነጋግረኝ" ይገኙበታል። እንዲሁ ዓይነቶቹን ብዙ ልታስደምጠን እያሰበች ባለችበት ሰዓት ላይ ነበር ሕይወት እንደማይፈታ ትብታብ ተወሳስቦባት ከመንገድ የቆመችው። ገና ስትመጣ የነገውን ትልቅ ተስፋ ቢጣልባትም ነገር ግን ሳይሆን ቀረ።

ቤተልሔም መኮንን ወደ ሙዚቃው በተቀላቀለችበት ሰሞን ገና የ17 ዓመት ልጅ ነበረች። በፊት ተጫዋችና በሥራም ይሁን በሌላው ፈጣንና ተግባቢም ነበረች። ትንሽ ሳለች ጀምሮ በባህሪዋ ብዙዎችም ይወዷታል። ነገሮችን መሞከርና ሁሌም ማንጎራጎር ሥራዋ ነበር። ሙዚቃውን ሳትጀምር አስቀድሞ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ውስጥም የድምጽ ተማሪ ነበረች። ከዚያ በኋላ ነበር አብረዋት ከተማሩት ጋር "አነጋግረኝ"ን ለመሥራት የተነሱት። ሙዚቃው በተለቀቀ ማግስት ሕይወት ለቤተልሔም እንደ መስከረም ጸሐይ ወገግ ብላ ፈነጠቀች። በአንድ ጊዜ የዝና ማማ ላይ ተሰቀለች። ሙዚቃው ተደምጦ አያበቃም ከየአቅጣጫው ይደጋገማል። ምቱ ዛሬም ድረስ ከብዙዎች ልብ ላይ እንዳለ አለ። በዚሁ ቀጥሎ ብዙ ራዕይ ብዙ ተስፋ ሰንቃ ነገንም እያሰበች ነበር። ሕይወት ባዳ ተስፋና ሕልምም ከሀዲ ናቸው፤ አንድ ቀን ክህደትን ይፈጽማሉ። ሁሉም እንዳልነበረ ሆኖ ሲቀርም እጅግ ያማል። የወጡበት ከፍታ መልሶ ያንኑ ያህል ሲፈጠፍጥ የጭለማውን ገደል መውጣት እጅግ ፈታኝ። የማለዳ ጸሐይ ለመምሰል የሚቻላት ሕይወት ከዚያ በበለጠም የምሽት ድቅድቅ ጭለማ መሆንን ትችልበታለች። ይህች ዓለምም በወረት የናወዘች መጥፎ ወረተኛ ናት። ማሸርገድም መሸርከትም ለሷ ቀላል ነው። ያቺ ፍንድቅድቋ አፍላ ወጣት እምብዛም በዚያ ሳትቆይ በሌላ አስፈሪ የሕይወት እረመጥ ውስጥ ገባች። ሀገሩ ሙሉ በእርሷ ሙዚቃ ዳንኪራውን ሲመታ እርሷ ግን በከባድ የአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ ነበረች። ዕለት ዕለት ስቃይዋ እየባሰ ሄዶ በጨለማው የሕይወት ዋሻ ውስጥ ወደቀች። በሙዚቃዋ በሰጠችው ደስታ ሌላው ሲፍነከነክ እርሷ ግን በመራራ የእንባና የሀዘን አጀብ ውስጥ ተሸጉጣ ነበር። አንዳችም ኑሮ ኑሮ፣ አንዳችም ሕይወት ሕይወት አይሸታትም ነበር። በዚያ ሰሞን የገጠማትን ነገር ማንም ልብ ብሎ ያስተዋለ አልነበረም። በማይነጋ የቀን ሌት ጭለማ ውስጥ መዘፈቋን ጠርጥሮ የፈለጋትም አንድም የለም። ከአቅሟ በላይ ሆነና ቤቲ የአዕምሮ ሕመምተኛ፣ የሕይወት ቁራኛ ሆነች።

"ቤቲ እኮ እየዘፈነች ነው አሉኝ። ደግሜ ብጠይቅ አዎ እየዘፈነች ነው አሉኝ። ከዚያም ዘሬን ተመልክተሽዋል የቄስና የመነኩሴ ልጅ ነኝ...ብዬ ብላት እማዬ በምትወጂው ገብርኤል ይዤሻለሁ እማዬ! ስትለኝ እኔም ተውኳት" አሉ የቤተልሔም ወላጅ እናት። አባቷ የሚኖሩት ከእነርሱ ተለይተው በመሆኑ ከልጅነቷ ጀምሮ ለማሳደግ በኑሮ ብዙ መከራን ያሳለፉባት ልጃቸው ናት። አሁን ደግሞ ቤተልሔም የሁለት ልጆችም እናት ናት። እናቷ ማንም የሌለበትን የሰቆቃ ዘመን ከእርሷ ጋር አሳልፈዋል። ድምጻዊቷን ከወዴት ገባች ምንስ ነካት ብሎ ፍለጋ የወጣ አልነበረም። ከረዥም ጊዜያት በኋላ ግን እናቷ ራማ በተሰኘ ሚዲያ ቀርበው የሆነችውን ሲናገሩ ተሰማ። በቃለመጠይቁም በአዕምሮ ሕመም ተይዛ ተኮራምታ ከቤት ውስጥ መቅረቷን ተናገሩ። "ቤቲ እኮ ጥሩ ልጅ ነበረች። ልጅ ሆና እንኳን እንደ ልጅ ይህቺን ታህል! ጫፏን ነክቻት አላውቅም ነበር። ሌሎቹን በሚጥሚጣ እያጠንኩ ነበር ያሳደኳቸው እሷን ግን... በሰፈር ውስጥ እንኳን ሰው ቀና ብላ የምታይ አልነበረችም። ግን እንዴት እንዳገኘብኝ አላውቅም!...እኔ ከሞትኩ ልጄን የቀን ጅብ ነው የሚበላብኝ፣ እሷ ጠዋት ከሞተች እኔ ማታ ልሙት ነው ፈጣሪዬን የምለው..." በማለት እንባ ከዓይኖቻቸው እየፈሰሰ ልባቸው በሀዘን እየደማ ብሶታቸው ገንፍሎ በእናት አንጀት እንዲያ ሲብሰከሰኩ ለተመለከተ ልብን የሚሰብር ነበር። ከደረሰባት ከአዕምሮ ሕመም በተጨማሪ ኩላሊቶቿም ከጥቅም ውጭ ስለመሆናቸው እናት ገልጸውታል። ከዚህ በኋላ የነበራት ሕይወትም በሕክምናና በፀበል የቆመ ነበር።

ቤተልሔም መኮንን "አነጋግረኝ"ን ባወጣችበት ሰሞን ጤንነት እየተሰማት አልነበረም። ተጫዋችና በሳቅ የሚጥለቀለቀው የልጅነት ፊቷም እንደቀድሞው የሚያበራ አልሆነም። አልፎ አልፎ ድንገት ውልብ የሚልባት ሀሳብና ጭንቀት ፊቱን አጥቁሮና እሳት ለብሶ ከፊቷ ላይ ድቅን ያለ ይመስላል። ሕይወትም መልኳን ቀይረችባት። ቤተልሔም በአዕምሮ ጭንቀት ተይዛ፣ የአዕምሮ ሕመምተኛ ሆነች። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከሙዚቃ ወዲያ እራቀች። ከደጅ ለመውጣት እንኳን አልቻለችም። ከቤት ውላ አድራ ከቤት ውስጥ ብቻ ቀረች። አጠገቧ የነበሩትና ስቃይዋን ሁሉ የተሸከሙት እናቷ ነበሩ። ከሕመሟ የተነሳ ማንነቷ ብቻም ሳይሆን መልክና ደምግባቷም ጭምር እርቋት ነበር። ጠቋቁራና አመዳይ ለብሳ ሌላ ሰው ሌላ ቤቲ ሆነች። በዚህ ወቅት ስሟ ገኖ ሀገር ምድሩ ቤቲ... ቤቲ እያለ የነበረ ቢሆንም፤ ነገር ግን በድንገት ከደጅ ላይ ወጥታ የተመለከታት ጎረቤት እንኳን ማን እንደሆነች አያውቅም ነበር። ምክንያቱም በሰዓቱ ባደገችበት ሰፈር ውስጥ ባለመሆኗ ሙዚቃው ላይ ያለችውን ወፍ መሳይ ባለማራኪ ድምጽዋን ልጅ እንጂ እንዲህ በአዕምሮ ሕመም ተይዛ የምትጎሳቆለዋን ቤተልሔም መኮንን የሚያውቅ አልነበረም። ያ ጊዜ ለእርሷ የሰቆቃ፣ ለእናት ደግሞ የመከራ ዘመን ነበር። ጥቂት ወዳጆቿና የሙዚቃ አጋሮቿ ሊረዷት ቢሞክሩም ጤንነቷን መልሶ ዳግም እርሷን ከሙዚቃ ጋር መመልከት የሚቻል አልነበረም። እነርሱም ተስፋ ቆርጠው ሳይደክሙ አልቀረም። አሁንም ከእናት ጋር ብዙ ሕመም... ብዙ ስቃይ...ብዙ የተከረቸመ መውጫ አልባ ሕይወት ቀጠለ...



ቤተልሔም መኮንን

ከዘመናት በኋላ ችግሯ አደባባይ ወጥቶ ብዙኀኑ አወቀላት። "ለማመን የሚከብድ የቤተልሔም መኮንን ሕይወት፣ ቤቲ አነጋግረኝ ምን የገጠማት..." እየተባለ ከብዙ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ ተራግቦም ነበር። ትልቁ ችግራችን አስቀድሞ መፈለግና ቀድሞ መድረስ ላይ ቢሆንም፤ ነገር ግን የአንዱን ችግር ከሰማንና ከተመለከትን በኋላ ግን ጆሮ ዳባ ብለን ለማለፍ የምንችል አይደለንም። አስታውሶ የጠፋን ያለመፈለግና የመርሳት አባዜ እንጂ በሰብአዊ ማንነታችን ላይ የመደራደር አቅሙ የሌለን፣ በሁለት በኩል የተጠፈጠፍን ምስኪኖች ነን፤ እኛ ኢትዮጵያውያን። ቤተልሔም መኮንን በሕመም መከረሟን የሰማ ሁሉ እርሷን ለመርዳት በየፊናው ያልተሯሯጠ አልነበረም። በሕክምና በነበረችበት ሰዓትም ኢትዮጵያዊነት ማለት መልካምነት ስለመሆኑ ያስመሰከሩ ብዙ ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ አንድ ዶክተርና ሌሎች ጥቂት ወዳጆቿ ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። አልጋ ይዛ ሕክምናዋን በመከታተል ላይ ሳለች ከውጭ እየተመላለሰ የሚያክማት አንድ ዶክተር ነበር። ወዳጆቿም ካሰባሰቡት ገንዘብ ለዶክተሩ ቢሰጡትም ገንዘቡን አልፈልግም በማለት "ወርም ይሁን ዓመት ሕክምናዋ የፈጀውን ጊዜ ያህል በራሴ ወጪ አክማታለሁ" በማለት ያለአንዳችም መታከት ሲረዳት ቆየ። ከዶክተሩ አልፎ ባለቤቱም ጭምር ድጋፍ ስታደርግ ነበር።

እጅግ ጭንቅ የበዛበት የመከራ ጊዜዋ ከሁሉም በተለየ በ2013 ዓ.ም ነበር። እርግጥ ነው በሕክምናው እንድትድን ከዶክተሩ ጀምሮ ብዙዎች የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት አድርገዋል። መልካምነት የተሞላበት ጥረት ሁሉ ስኬታማ ይሆናል ማለት አይደለም። ስኬታማ አለመሆኑም በጎ አድራጊውን ከበጎነቱና ከልፋቱ ዋጋን አያስቀንስበትም፤ ማድረግ ያለብንን የግል ድርሻችንን እስከተወጣን ድረስ ሁሌም መልካም ሁሌም ስኬታማ ነን። ቀሪው የሕይወትና የሕይወት ሠሪው ፈንታ ናቸው። በሕክምናው በነበረው ርብርብ ውጫዊ አካሏን እንጂ መንፈስና ማንነቷን ለማግኘት በጣሙን አስቸጋሪ ሆነ። ከዚህ በኋላ ቤተልሔም በቀጥታ ወደ አንጎለላ ተወሰደች። በዚያም በገዳም ውስጥ እንድትሰነብት ተደረገ። ወደ ሰሚነሽ ኪዳነምህረት ገዳም ገባች። ከ6 ወራት በላይ በእምነቷ አጽንታ ፀበሉን ስትወስድና እምነቱን ስትቀበልም ቆየች። ከዚያ በኋላ ነበር በአንድ ወቅት በኢቢኤስ የቴሌቪዥን ጣቢያ ቀርባ "አሁን ደህና ነኝ። ችግሬን ተረድታችሁ በገንዘብና በጸሎት አብራችሁኝ ከጎኔ ለቆማችሁ መልካም ወዳጆቼና መልካም አድራጊዎች በሙሉ ከልቤ አመሰግናለሁ። ውለታችሁን ሁሉ እርሱ ፈጣሪ ይመልስላችሁ" ስትል በደስታ ተሞልታ ወደ ጤንነቷ ስለመመለሷ ተናገረች። የእርሷ ወደ ጤንነቷ መመለስ ከማንም በላይ ለእናት ዳግም ውልደት ነበር። ያለ እንቅልፍ ያደሩባቸውን ሌሊቶች እያስታወሱ ከዚያ የልብ ስብራትና እንባ ተመልሰው በፈገግታ ቆሙ።

"...ብድር ይግባችሁ! ልጄም ደህና ሆና በጣም ጥሩ ለውጥ ነው ያየሁት። ከአሜሪካን ሀገር ብቻ ወደ 4 መቶ 50 ሰው ነው የደወለው። ከእንግሊዝ፣ ከጣሊያን የሰማ ሁሉ ከየሀገሩ እየደወለ ይጠይቃል። ሕዝቡ አሁን በቃ መደወል... መደወል ነው። ቤተልሔም መኮንን ግርማ እንወዳታለን፣ እናደንቃታለን፣ ልንረዳት እንፈልጋለን ነው። ሙስሊሙም ክርስቲያኑም፣ ቀንቋውን የማይችለው ሁሉ ይደውላል። ስልኩ ሲጮህ ውሎ እንዲህቹ በሱ ተጠምጄ ሃሎ! ስል...ሃሎ! ስል ምግብ እንኳን ሳልበላ ጾሜን የዋልኩት ቀንም አለ" ሲሉ በደስታ ከምስጋና ጋር ቀርበው ታዩ። ቤተልሔም በሕመም በነበረችባቸው ጊዜያቶች እናቷ የተሸከሙትን አይቶና ሰምቶ፣ እንደ ሻማ እየቀለጡ በመስዋዕትነት ከቆሙበት ጨለማ አልፈው ዛሬ እንዲህ ለመታየት የሚበቁ አይመስሉም ነበር። "...ለእናቴ ቤት ገዝቼ ከፎቅ ላይ እሰቅላለሁ አልኩ እንጂ፣ መኪና ገዝቼ አንቺን ከገዳም አዞራለሁ ስል አስብ ነበር እንጂ፤ አንድም ቀን ጥርስና አይንሽን አጠፋለሁ፣ ላንቺ ስቃይ ሆኜ እንደዚህ እጎዳሻለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ...እናቴ ይቅር በዪኝ! ብላ ከጉልበቴ፣ ከጫማዬ ስር ተደፍታ አለቀሰች። እናቴ ገደልኩሽ ብላ ከስንት ዘመን በኋላ በዚህ ሰሞን ሳመችኝ። እኔም በጣም ደስ አለኝ!" በማለትም ከሕመሟ ካገገመች ወዲህ ስላሳየችው ትልቅ የማንነት ለውጥ አብስረዋል።

"አሁን ወደ ሥራዬ ለመመለስ እፈልጋለሁ። ከራቁት ሕዝብና የሙዚቃ አፍቃሪ ወዳጆቼ ጋር ዳግም ለመገናኘት እፈልጋለሁ። ግጥምና ዜማም የምሞክር ብሆንም በሥራው ደግፈው ከጎኔ ለመቆም የሚችሉ የሙዚቃ ባለሙያዎች ያስፈልጉኛል። በየትኛውም በኩል ሥራዎቻቸውን ሊሰጡኝና አብረውኝ ሊሠሩ ለሚፈልጉ ሁሉ እኔ ዝግጁ ነኝ" ስትል በቅርቡ ሚዲያ ላይ ቀርባ የቀጣይ ሕልሟን አጫውታለች። አሁን ሁሉም ነገር ሠላም የሆነ ይመስላል። ያጎደለችውን የጥበብ አካል መልሳ ሙሉ አድርጋዋለች። ደረቁ የሕይወት በጋ አልፎ ክረምቱም ይመጣል። የደረቀች ጽጌረዳም ትለመልማለች። ትላንት የተለየ፣ ዛሬም እራሱን፣ ነገም ሌላ ቀን ነው። ከእርሷም ብዙ ሌላ እንጠብቃለን።

# ዓለም አቀፍ



## ቻይናና ሩሲያ የባሕር ኃይሎች የጋራ ወታደራዊ ልምምድ አደረጉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቻይና እና የሩሲያ የባሕር ኃይሎች የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ማድረግ መጀመራቸው ተነግሯል።

ቻይና እና ሩሲያ በደቡብ ቻይና ዣንጂያንግ ከተማ አቅራቢያ በሚገኝ በውሃ እና በአየር ክልል ላይ የጋራ የባሕር ኃይል ልምምዶችን እያደረጉ መሆኑን ሰሞኑን አስታውቀዋል።

“የጋራ ባሕር-2024” በሚል መጠሪያ የተሰጠው ልምምዱ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ እንደሚቆይ የቻይና መከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የሁለቱ ሀገራት የባሕር ኃይል የጋራ ልምምድ ላይ አውዳሚው የጋይድድ ሚሳዔልን ጨምሮ ሌሎችም ግዙፍ መሣሪያዎችን የታጠቁ የጦር መርከቦች እንደተሳተፉ ነው የተገለጸው።

የቻይና መከላከያ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ዣንግ ዢያኦጋንግ “ልምምዱ ሁለቱ ወገኖች የባሕር ላይ የፀጥታ ስጋቶችን በጋራ ለመቅረፍ እንዲሁም ዓለም አቀፍ እና ቀጣናዊ ሠላምና መረጋጋትን ለማስፈን ያላቸውን ቁርጠኝነት እና አቅም ለማሳየት ያለመ ነው” ብለዋል።

ልምምዱ በሁለቱ ሀገራት መካከል የተደረሰው መደበኛ የመከላከያ ትብብር አካል መሆኑንም ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

አዲሱ የባሕር ኃይሎች ልምምድ “በአዲሱ ዘመን የቻይና-ሩሲያ አጠቃላይ ስትራቴጂካዊ የትብብር አጋርነትን የበለጠ ያጠናክራል” ብለዋል ዣንግ።

የቻይና እና የሩሲያ የባሕር ኃይሎች የጋራ ወታደራዊ ልምምድ የታወጀው በዋሽንግተን በተደረገው የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃልኪዳን (ኔቶ) ስብሰባ መጠናቀቁን ተከትሎ ነው።

በዋሽንግተኑ የኔቶ ስበሰባ ላይ የተሳተፉ ሀገራት በቻይናና በሩሲያ መካከል ያለው ስትራቴጂካዊ አጋርነት እንዲሁም ሁለቱ ሀገራት ለመፍጠር እየሠሩት ያለው አዲስ የዓለም ሥርዓት ትልቅ ስጋትን የሚደቅን መሆኑን መግለጻቸው ይታወሳል።

ቻይና የኔቶ መግለጫ “በቀዝቃዛው ጦርነት አስተሳሰብ እና በጦር አነጋገር የተሞላ ነው” ስትል ተችታለች።

## አዲሱ የኢራን ፕሬዚዳንት የአሜሪካን ጫና እንደማይቀበሉ ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲሱ የኢራን ፕሬዚዳንት መሱድ ፔዝሽኪያን ኢራን ለአሜሪካ ጫና ሽብረክ እንደማትል ተናግረዋል።

ሀገራቸው ከቻይና እና ሩሲያ ጋር ያላትን ግንኙነት ያነሱት ፕሬዚዳንት መሱዱ ፔዝሺኪያን ኢራን ከአሜሪካ የሚመጣ ጫናን አትቀበልም ብለዋል።

በሄሊኮተር አደጋ የሞቱትን ራይሲን ለመተካት በተካሄደው ምርጫ፣ ወግ አጥባቂውን ያሸነፉት እና በአንጻራዊነት ለዘብተኛ የተባሉት ፔዝሺኪያን ኢራን የኑክሌር ጦር መሣሪያ እንደማትፈልግ እና ከጎረቤቶቿ እና አውሮፓ ጋር መነጋገር እንደምትፈልግ ተናግረዋል።


“አሜሪካ...እውነታውን መቀበል አለባት፤ የኢራን መከላከያ አስተምህሮ የኑክሌር ጦር መሣሪያ እንደማያካትት ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጋዜ መረዳት አለባት” ብለዋል “ለመላው ዓለም የተላለፈ መልእክት” በሚል ርዕስ ባወጡት መግለጫ።

የ69 ዓመቱ የልብ ጠጋኝ የሆኑት ፔዝሽኪያን ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንደሚከተሉ እና በ2015 የኑክሌር ስምምነት ምክንያት ከኃያላን ሀገራት ጋር የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

ነገር ግን በሀገሪቱ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው አያቶላህ አሊ ካሚኒ በመሆናቸው፣ ኢራናውያን ፔዝሽኪያን በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የገቡትን ቃል ስለመፈጸማቸው ይጠራጠራሉ።

ፔዝሽኪያን “ቻይና እና ሩሲያ ፈታኝ በሆነ ጊዜ ከጎናችን ቆመዋል። ለወዳጅነታቸው ከፍ ያለ ዋጋ እንሰጣለን” ብለዋል።

“ሩሲያ ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጣት ጎረቤት እና ስትራቴጂካዊ አጋራችን ነች፤ አዲሱ አስተዳደርም



መሱድ ፔዝሽኪያን

ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል” ያሉት ፔዝሽኪያን ቴህራን በዩክሬን ያለው ጦርነት እንዲበቃ የሚደረገውን ጥረት ትደግፋለች ብለዋል።

ፔዝሽኪያ “የኢራን ሕዝብ መብታችንን እና ጥቅማችንን አስከብረን” በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ እንደሚፈልግ ገልጸዋል።


Development Bank of Ethiopia

# Invitation for National Competitive Bid (NCB)

## Bid Ref. No:- DBE/NCB/S/01/2024/25

1. Development Bank of Ethiopia invites interested and potential bidders for tie procurement of **Proposal for Construction input Material, Labour & Equipment Cost/Price Supply Service.** Therefore Interested bidders are required to submit together with their bid documents;

i. Renewed trade license IV. Tax clearance certificate

ii. TIN Certificate

iii. VAT Registration Certificate

2. Interested bidders shall Purchase complete set of bidding documents beginning from **July 15, 2024** upon payment of a non-refundable **Birr300** (Birr Three hundred only) to Corporate Branch, Tower II, Ground floor and collect the bid document Soft Copy from Procurement Directorate, Office No.104 , Tower III,1st floor.

| S/No | Types of procurement | Bid security required | Remarks |
|---|---|---|---|
| 1 | Proposal for Construction input **Material,Labour & Equipment Cost/Price Supply Service** | 25,000 | CPO or unconditional bank guarantee from recognized bank |

3. Bids shall be submitted into the tender box prepared for this purpose on or before **July 30, 2024 at 10:00 A.M (in the morning)** at the **Development Bank of Ethiopia Head Office Tower III, 1st floor.**
4. The Bid's shall be opened on the above mentioned address, on **July 30, 2024 at 10:05 A.M (in the morning)** in the presence of bidders and/or their authorized representatives.
5. Interested bidders may obtain further information from DBE Head Office, Procurement Directorate, Tower III, 1st floor, Tel. +251 11 5578088, ext. 364/805;
6. Bidders should present their Financial and Technical documents with 2 copies separately in the sealed envelope.
7. The language of Tender shall be English.
8. DBE reserves the right to accept or reject any or all bids.

# Development Bank of Ethiopia

# ስፖርት





## ‹‹ጦሩ››- የኢትዮጵያ ስፖርት የጀርባ አጥንት

**ብርሃን ፈይሳ**

በ1936 ዓ.ም የተመሠረተው እና ሀገራቸውን ወክለው በተለያዩ ዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች መወዳደር የቻሉ ብርቅዬ ጀግና አትሌቶችን፣ እግር ኳስ ተጫዎቾችን እና ሌሎች ስፖርተኞችን ማፍራት የቻለ የማይረሳ ታሪክ ያለው አንጋፋ ክለብ ነው፣ መቻል። ለሰማንያ ዓመታት አንጋፋነቱን አስጠብቆ የዘለቀ በየጊዜው ዘመን ተሻጋሪ ታሪክ ሠሪዎችን በታሪክ ማኅደር አስፍሮ ዛሬም በሀገራችን የስፖርት ዘርፍ የበኩሉን ዐሻራ እያሳረፈ ነው።

ከኢትዮጵያ ዘመናዊ ስፖርት ጋር እኩያ ሊባሉ ከሚችሉ ክለቦች መካከል መቻል ተጠቃሽ ነው። የሃገርን ዳር ድንበር ከማስጠበቅ ባለፈ በዓለም አቀፍ አደባባይ የስኬት ታሪክን የሚጋራው ጦሩ ዘመናትን ተሻግሮ ዛሬም ድረስ ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት በመትጋት ላይ ይገኛል። በ1936 ዓ.ም. ምሥረታውን ያደረገው አንጋፋው መቻል የ80ኛ ዓመት በዓሉን ባለፈው አንድ ወር ‹‹መቻል ለኢትዮጵያ›› በሚል መሪ ሃሳብ በተለያዩ መርሐ ግብሮች እያከበረ ዛሬ በድምቀት ያጠናቅቃል።

‹‹ጦሩ›› የሚል ቅጽል የሚታወቀው ክለቡ እንደየወቅቱ ጠቅል፣ መቻል፣ ፋና፣ ፀሐይ ግባት፣ መከላከያ፣ ማዕከላዊ ዕዝ፣ ጦር ሠራዊት፣ ምድር ጦር፣ አየር ኃይል፣ ባሕር ኃይል፣ …የሚሉ መጠሪያዎችም ነበሩት። ከምሥረታው ጥቂት ዓመታት በኋላ ከ1948 አንስቶ በተለያዩ ስፖርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች በመሳተፍም ራሱን ብቻ ሳይሆን ሃገርንም ያስጠራና አሁንም በዚያው ሁኔታ ለመቀጠል በጥረት ላይ ያለ ክለብ ነው።

በተለይ በአትሌቲክስ እና እግር ኳስ ስፖርቶች ዘመናትን የተሻገረ ዝናን የገነባ ቢሆንም፤ መረብ ኳስ፣ ቦክስ፣ ብስክሌት፣ ቅርጫት ኳስ፣ እጅ ኳስ፣ ውሃ ዋና፣ ጠረጴዛ ቴኒስ እና ክብደት ማንሳት ስፖርቶችም በውድድሮች ላይ ይካፈል ነበር። ከሜልቦርን ኦሊምፒክ አንስቶ ኢትዮጵያን በመድረኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ ያስጠራው ሻምበል አበበ ቢቂላን ጨምሮ፤ ባሻዬ ፈለቀ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩፅ ይፍጠር፣ እሸቱ ቱራ፣ ቶሎሳ ቆቱ፣ መሐመድ ከድር እና ሃዲስ አበበን የመሳሰሉ አትሌቶች የውትድርናው ዓለም ለኢትዮጵያ ያበረከታቸው ቀደምት ዕንቁዎች ናቸው። አሁንም አትሌት ኢማና መርጋ፣ አሊ አብዶሽ፣ ሱሌ ኡቱራ፣ ደረሰ መኮንን፣ ድሪባ ጋሪ፣ አልማዝ አያና፣ ሙክታር እድሪስ፣ ፀጋዬ ከበደ፣ ቲኪ ገላና፣ ኢብራሂም ጄይላን፣ ጌታነህ ሞላ እና ሃዊ ፈይሳን የመሳሰሉ አትሌቶች ባለቤት ነው ክለቡ።

መቻል በእግር ካሱ በተለይም በ1989 ዓም የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ፌስቲቫል መካሄዱን ተከትሎ ተጫዋቾችን በማሰባሰብ በ1990 ዓ.ም. መከላከያ በሚል ስያሜ በድጋሚ ተዋቀረ። በአዲስ መልክ ሁለተኛ ዲቪዚዮን ላይ ቢጫወትም በዚያው ዓመት ሻምፒዮን በመሆኑ ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ሊያድግ ችሏል። እስከ 1993 ዓም ባለው ጊዜም ፋና እና ፀሐይ ግባት በሚል ስያሜ በድጋሚ ተከፍሎ በብሔራዊ እና ከፍተኛ ሊግ ሲጫወቱም ቆዩ። በ1996 ዓ.ም. ድጋሚ ክለቦቹ መከላከያ በሚል ተዋሕዶ በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ተሳትፎውን ጀመረ።

የመቻል ዋናው እግር ኳስ ቡድን በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አዲሱ ፎርማት ለረጅም ዓመታት ከቆዩት ክለቦች መካከል አንዱ ሊሆን ችሏል። በእነዚህ ዓመታትም ባለፈው ሳምንት ሁለተኛ ሆኖ የጨረሰበት ውጤት ከፍተኛው ቢሆንም በደረጃ ሰንጠረዡ መካከለኛ ስፍራ ላይ የሚቀመጥ ክለብ ነው። በተለይ ከሊጉ ተሳታፊዎች ክለቡን ለየት




**አንጋፋው መቻል 80ኛ ዓመት ክብረበዓሉን ዛሬ ያጠናቅቃል፣**

የሚያደርገው አንድም የውጪ ተጫዋች ባለማስፈረምና በሃገር ውስጥ ተጫዋቾች ብቻ በመገልገሉ ነው። የግብ ጠባቂ እጥረት ያለበት የኢትዮጵያ ወንዶች ብሔራዊ ቡድን ለዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚያማትረው ወደዚሁ ክለብ ነው። ለአራት ጊዜያት ያህልም የኢትዮጵያ ጥሎ ማለፍ ሻምፒዮን በመሆን ለአራት ጊዜ በአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ተሳታፊ መሆኑ አንዱ ስኬቱ ነው።

የስፖርታዊ ጨዋነት ችግር ለዓመታት በነገሠበት ወቅት የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ስሙ ሳይነሳ የቆየውም መቻል ነው። እንዲያውም ስፖርታዊ ጨዋነትን በማስፈን ረገድ ተጫዋቾች የሚወጡት ሚና የሚያስመሰግን ነው።

ስለ መቻል ሲነሳ ብዙ ጊዜ የምንሰማው በሁሉም ዓይነት ማለትም እግር ኳስን ጨምሮ በአትሌቲክስ የተለያዩ ርቀቶች ሀገራቸውን ወክለው በሁለቱም ፆታ በድል የደመቁ ስፖርተኞችን ነው። ይህ ተደጋግሞ መነሳቱ መልካም ሆኖ ሳለ ከተወዳዳሪና ባለድሎች ባሻገር በርካታ የስፖርት ፈርጥ የሀገር ገጸ-በረከት የሆኑ የስፖርት ባለሙዎችን በማፍራት ረገድ ጉልህ ሚና አለው።

ከአሠልጣኞች ጀምሮ በሁሉም የስፖርት ዓይነት በእያንዳንዷ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች የስፖርት ጠቢባን የሆኑ ሙያተኞችን መቻል ስፖርት ክለብ በማፍራት ከራሱ አልፎ ለሀገር ትልቅ ውለታ ውሏል እየዋለም ይገኛል።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት አቶ ጥላሁን ጌታቸው እና በፍ/ባለዕዳ እነ ወ/ሮ ሰናይት ተገኝ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 196061 በ6/7/2016 ዓ.ም እና በኮ/መ/ቁ 198675 በ29/08/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 237/0155 በካ/ቁ/12/27/5737/00 በወ/ሮ ጠንፌለሽ አክሊሉ ስም የተመዘገበ የይዞታው ስፋት 144 ካ/ሜ የሆነው ቤት የሐራጅ መነሻ ዋጋ ብር 5,929,824 (አምስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሃያ አራት ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሐሴ 10 ቀን 2016 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ 4፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ሰዓት ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4 ኛው አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አፈ/ዳ/ ስም CPO አሰርቶ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት። የፍ/አፈ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሐራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን።

**በፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**



ሲቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ
CITY UNIVERSITY COLLEGE

## የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

የሲቲ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 13 ኛ አስቸኳይ ጉባዔ ከዚህ በታች በተመለከቱት አጀንዳዎች መሠረት ቅዳሜ ነሃሴ 04 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ ሺ-ሰማኒያ በሚገኘው በማህበሩ ዋና ፅ/ቤት ስለሚካሄድ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በተባለበት ቀንና ቦታ ተገኝተው በጉባኤው ላይ እንዲሳተፉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል።

በስብሰባው ላይ ለመገኘት የማይችል ባለአክሲዮን ከጉባኤው ዕለት ቢያንስ 3 ቀናት አስቀድሞ በማህበሩ ጽ/ቤት በመገኘት የውክልና ቅፅ በመሙላት ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን በስብሰባው ዕለት ራሱ መገኘት የማይችል ባለአክሲዮን ህጋዊ የውክልና ሰነድ የያዘ ወኪል በሰዓቱ /በስብሰባው ዕለት/ መላክ የሚችል መሆኑን እንገልፃለን።

**1. መደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ፡**

1.1 የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለመሾም፤

**2. 13ኛ አስቸኳይ ጉባዔ አጀንዳዎች**

2.1 የማህበሩን ካፒታል ስለመጨመር፤

2.2 የማህበሩን የመመስረቻ ፅሁፍ ስለማሻሻል፤

**አድራሻ፡**- ንግስት ኤልሳቤት መንገድ፣ ከአራት ኪሎ ወደ መገናኛ በሚወስደው መንገድ ራስ አምባ ሆቴል አጠገብ፣

**ስልክ ቁጥር፡- +251-011-12-33 212 +251-916-58-73-47/**

**ሲቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አ/ማህበር**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**